# ምዕራፍ ፸፪
## ጉባኤ

፩ ፤ ወድኅሬሁ : ለዝ : ትእዛዝ : ርኢኩ : ካልአ : ትእዛዘ : ለብርሃን : ንእስ : ዘስሙ : ወርኅ ፤
ትእዛዘ ፤ ካለ : ዘብርሃን ፤ለብርሃንም : ካለ : ትእዛዞ : ቢል : በቀና : ነበር ፤ የፀሐይን : አካሄድ ፤ የፀሐይን : ሥርዓት ፤ ካየሁ : በኋላ ፤ ከፀሐይ : የሚያንስ : የጨረቃን : ትእዛዝ : የጨረቃን : ሥርዓት : አየሁ ፤
፪ ፤ ወክበቡ : ከመ : ክበበ : ፀሐይ ፤ ሰሌዳው : እንደ : ፀሐይ : ሰሌዳ ነው ፤ ትክክል : ናቸውና ፤ አንድም : ከመ : ክበበ : ሰማይ : ሲል : ነው ፤ ክብነቱም : እንደ ሰማይ : ክብ : ነው ፤ የማናው ቀውን : በምናውቀው : ተረጉመው ፤ አንድም : ብርሃን : እየተነሳው : ሰማይ : መስሎ : ይታያልና ፤
ወሠረገላ : ዚአሁ : በኀበ : ይፂዓን : ነፋስ : ይነፍሕ ፤
ወደሠረገላው : በሚወጣበት : ጊዜ : ነፋስ : ይነፍሳል ፤ ሠረገላ : የሚለው : ርጉዕ : ነፋስን ነው ፤ ይነፍሕ : የሚለው ፤ ዝርው : ነፋስን : ነው ፤ ሠረገላውን : የሚያፋጥን : ነው ፤

፫ ፤ ወበመስፈርት : ይትወሀብ : ሎቱ : ብርሃን ፤
በልክ ፤ በመጠን ፤ ብርሃን : ይሰጣል ፤ በምላት : እስከ: ፲፭ ቀን እየተጨመረለት ፤ እስከ : ፲፬ : ቀን : እየተነሳው ፤ ፳፱ ቀን : አብርቶ : በ፴ኛው : ቀን : ጠፍ: አድሮ : በ፴፩ኛው : ሠርቅ : ያደርጋል ፤ በሕፀፁ : እስከ : ፲፬ ቀን: ብርሃን : እየተጨመረለት : እስከ : ፲፬ : ቀን : እየተነሳው ፳፰ ቀን : አብርቶ : በ፳፱ነኛው ጠፍ : አድሮ : በ፴ኛው : ሠርቅ : ያደርጋልና ፤
፬ ፤ ወበዘሆሉ : ወርኅ : ሙፃኢሁ : ወሙባኢሁ : ይትዌለጥ ፤
በወሩ : ሁሉ : የጨረቃ : መውጫው : መግቢያው : ይለወጣል ፤ በ፩ ኖኅት : ፩ ቀን ፤ በ፩ : ኖኅት : ፪ ቀን ፤ በ፩ : ኖኅት : ሦስት : ቀን፤ በ፩ : ኖኅት : ፯ ቀን ፤ በ፩ : ኖኅት : ፰ ቀን ፤ ይወጣልና ፤ አንድም : ብርሃኑ : ወደ : ሰሌዳው : የሚገባበት : የሚወጣበት : ቀን ይለወጣል ፤ በምላት : እስከ : ፲፭ኛው : ቀን : ብርሃን : እየተጨመረለት ፤ እስከ : ፲፬ኛው : ቀን : ብርሃን : እየተ

ነሳው ፤ ፳፱ ቀን : አብርቶ : በ፴ኛው : ቀን : ጠፍ : አድሮ ፤ በ፴፩ኛው : ሠርቅ : ያደርጋልና፤ በሕፀፁ : እስከ ፲፬ : ቀን : ብር ሃን : እየተጨመረለት : እስከ ፲፬ ቀን : እየተነሳው : ፳፰ : ቀን: አብርቶ : በ፳፱ነኛው : ጠፍ : አድሮ : በ፴ : ቀን : ሠርቅ : ያደርጋልና ፤

ወመዋዕሊሁኒ : ከመ : መዋዕለ : ፀሐይ ፤

ቀኑም : እንደ : ፀሐይ : ቀን : ነው : ጠፉን : ጨምሮ : ቈጥሮ : ፴: ቀን : ይሆናልና ፤

፮ ፤ ወሶበ : ይዔሪ : ከዊነ : ብርሃኑ : ይከውን : ብርሃኑ : ፯ተ : እደ : እም ብርሃነ : ፀሐይ ፤

ነገ : ከሚቀበለው : ክፍለ : ብር ሃን : ጋራ : ዛሬ : የሚቀበለው: ብርሃን : በተካከለ : ጊዜ : ከፀ ሐይ ፯ እጅ : ብርሃን : ተቀብሎ: የሚያበራ : ይሆናል ፤ የፀሐይን ብርሃን : ከ፯ ክፍሎ : ፯ተኛዪ ቱን : ከ፲፬ት : ክፍሎ : ሠርቅ ባደረገ : ጊዜ : አንዱን : ክፍል ይቀበላል ፤ አንድም : የሰሌዳው ብርሃን : አከዋወን : በተካከለ : ጊዜ : መላው : ሰሌዳው : ብር ሃን : በተሳለበት : ጊዜ : ሳብዓየ እደ : ይላል ፤ የፀሐይን : (ከፀ ሐይ) : ፯ኛውን : እጅ : ተቀብሎ : የሚያበራ : ይሆናል ፤ ሠርቅ : ባደረገ : በ፲፬ተኛው : በ፲፭ተኛው : ቀን : ነው ፤

፯ ፤ ወከመዝ : ይሠርቅ ፤

በሠርቅ : ጊዜ : ፯ተኛዪቱን : ክፍለ : ብርሃን : ተቀብሎ ፤ በምልዓት : ቢሉ : የፀሐይን : ፯ኛውን : ክፍለ : ብርሃን : ተቀ ብሎ : እንዲህ : ሁኖ : ይወጣል ፤

ወርእሱ : ዘመንገለ : ጽባሕ : ይወ ፅእ : በሠላሳ : ጽባሕ ፤

በሠላሳኛው : ቀን : በምዕራብ : ሰሌዳው : ብርሃን : ተቀብሎ : ማጭድነቱ : ወደ : ምሥራቅ : ሁኖ : ይወጣል ፤

፯ ፤ ወበይእቲ : ዕለት : ያስተርኢ ፤ በ፴ኛው ፤ አንድም : በ፴፩ኛው : ሠርቅ : ሁኖ : ይታያል ፤

ወይከውን : ለክሙ : ርእሰ : ወርኅ ፤ ለናንተም : ሠርቀ : ወርኅ : ይሆንላችኋል ፤

፰ ፤ ሠላሳ ፤ ፅባሓ : ምስለ : ፀሐይ: በኆኅት : እንተ : ይወፅእ : ፀሐይ ፤ በሠላሳኛው : ቀን : ነግሀ : ሠርቅ: ሊያደርግ : በሃያ : ዘጠነኛው : ቀን : ፀሐይ : በሚወጣበት : ደጃፍ : ለመውጣት ፤ ከፀሐይ : ጋራ : ያድራል ::

፱ ፤ ወመንፈቁ : ርኁቅ : ሰብዓቱ : እድ : ፩ዱ ፤

፯ት ፡ ክፍለ ፡ ብርሃን ፡ የሚሳ ልበት ፡ እኩሌታው ፡ አንዱ ፡ ወገን ፡ ከብርሃን ፡ የራቀ ፡ ነው ፤

ወኵሉ ፡ ክበበ ፡ ዚአሁ ፡ በከ ፡ ዘአ ልቦቱ ፡ ብርሃን ፣

፯ቱ ፡ ክፍለ ፡ ብርሃን ፡ የሚሳ ልበት ፡ ሰሌዳው ፡ ብርሃን ፡ የሌ ለው ፡ ባዶ ፡ ሰሌዳ ፡ ነው ፤

ዘእንበለ ፡ ሳብዒት ፡ እደ ፡ ዚአሁ ፡ እም፲ቱ ፡ ወ፩ቱ ፡ እደ ፡ ብርሃኑ ፣

ከ፲፩ቱ ፡ ክፍለ ፡ ብርሃን ፡ ፯ኛው ሳይቀር ፡ ከብርሃን ፡ የራቀ ፡ ነው ፣ በጠፉ ፡ ነው ፤ አንድም ፡ የቀረው ፡ አይለወጥም ፣ ዘእን በለ ፡ ሳብዒት ፡ ከ፲፩ቱ ፡ ክፍለ ብርሃን ፡ ከ፯ኛው ፡ በቀር ፡ ከብርሃን ፡ የራቀ ፡ ነው ፤ በሠ ርቅ ፡ ጊዜ ፡ ነው ፤ አንድም ፡ ፯ት ፡ ክፍለ ፡ ብርሃን ፡ የሚሳል በት ፡ እኩሌታው ፡ አንዱ ፡ ወገን ፡ ከጨለማ ፡ የራቀ ፡ ነው ፤ ወኵሉ ፡ ክበቡ ፡ ሰባት ፡ ክፍለ ፡ ብርሃን ፡ የሚሳልበት ፡ ሰሌዳው ፡ ከጨለማ ፡ የራቀ ፡ ነው ፤ ዘእን በለ ፡ ሳብዒት ፣ ከ፲፩ቱ ፡ ክፍለ ፡ ብርሃን ፡ ፯ኛው ፡ ሳይቀር ፡ ከጨ ለማ ፡ የራቀ ፡ ነው ፣ በምልዓት ፡ ጊዜ ፡ ነው ፤

፲ ፤ ወበዕለተ ፡ ይነሥእ ፡ ሳብዓየ ፡ እደ ፡ መንፈቀ ፡ ብርሃኑ ፤

ነግሀ ፡ በሚቀበለው ፡ ክፍለ ፡ ብር ሃን ፡ መጠን ፡ ዛሬ ፡ ፯ ፡ እጅ ፡ ክፍለ ፡ ብርሃን ፡ ከሚቀበልበት ቀን ፡ አስቀድሞ ፤

ይከውን ፡ ብርሃኑ ፡ ፯ቱ፣ ወ፯ቱ ፡ እድ አሐቲ ፤

፯ት፤ ፯ት ፡ ክፍለ ፡ ብርሃን ፡ የሚሳልበት ፡ ሰሌዳው ፤

ወመንፈቃ ፤

ያልተካከለ ፡ ነው ፤ ወመንፈ ቆሙ ፡ ናፈቁ ፡ እንዲል ፣ ፯ኛ ዪቱን ፡ ለ፯ኛው ፡ መንፈቅ ፡ ብሎ ታል ፣ ፯ኛው ፡ ክፍለ ፡ ብርሃን ፡ የሚሳልበት ፡ አንዱ ፡ ወገን ፡ ከብ ርሃን ፡ የራቀ ፡ ነው ፤ በጠፉ፤ አንድም ፡ በዕለተ ፡ ይነሥእ ፡ ሳብዓየ ፡ እደ ፡ ይላል ፣ በፀሐይ ክፍለ ፡ ብርሃን ፡ መጠን ፡ የፀ ሐይ ፡ ፯ኛውን ፡ እጅ ፡ በሚቀ በልበት ፡ ቀን ፡ ፯ት ፡ ፯ት ፡ ክፍለ ፡ ብርሃን ፡ የ፯ቱን ፡ ቀን ፡ እኩ ሌታ ፡ የ፯ኛው ፡ ክፍለ ፡ ብርሃን ፡ የሚሳልበት ፡ አንዱ ፡ ወገን ፡ ሰሌዳው ፡ ከጨለማ ፡ የራቀ ፡ ነው ፡ በምልዓት ፤

፲፩ ፤ ወየዐርብ ፡ ምስለ ፡ ፀሐይ ፣

ጨረቃ ፡ ነግሀ ፡ ሠርቅ ፡ ሊያደርግ ፡ ዛሬ ፡ ከፀሐይ ፡ ጋራ ፡ ይገባል ፤

ወሶበ ፡ ይሠርቅ ፡ ፀሐይ ፡ ይሠርቅ ፡ ወርኅ ፡ ምስሌሁ ፤

ፀሐይ ፡ በምዕራብ ፡ ገብቶ ፡ በሰ
ሜን ፡ ዙሮ ፡ በምሥራቅ ፡ በወጣ፡
ጊዜ ፡ ጨረቃም ፡ ይወጣል ፤
ወይነሥእ ፡ መንፈቀ ፡ እደ ፡ ብርሃን ፤
ባ፲ት ፡ ባ፲ት ኬክሮስ ፡ ፯ት፡፯ት
ክፍለ ፡ ብርሃን ፡ ይቀበላል ፤
፲፪ ፤ ወበይእቲ ፡ ሌሊት ፡ በርእሰ ፡
ጽባሐ ፡ ዚአሁ ፡ በቅድመ ፡ ዕለቱ ፡
ለወርኅ ፤
በርእሰ ፡ ጽባሐ ፡ ዚአሁ ፡ በቅ
ድመ ፡ ዕለቱ ፤ አንድ ፡ ወገን ፤
ነግሀ ፡ ሠርቅ ፡ ከሚያደርግበት ፡
ቀን ፡ አስቀድሞ ፡ በዚያች ፡
ሌሊት ፤
የዐርብ ፡ ወርኅ ፡ ምስለ ፡ ፀሐይ ፤
ጨረቃ ፡ ከፀሐይ ፡ ጋራ ፡
ይገባል ፤
፲፫ ፤ ወይጸልም ፡ በይእቲ ፡ ሌሊት ፡
፯ቱ ፡ ወ፯ቱ ፡ እድ ፡ ወንፍቃ፤
በዚያችም ፡ ሌሊት ፡ ሰባቱ ፡
ክፍለ ፡ ብርሃን ፡ የ፯ቱ ፡ እኩሌታ፤
፯ኛው ፡ ክፍለ ፡ ብርሃን ፡ የሚ
ሣልበት ፡ ስሌዳው ፡ ፲፪ት፡ ሰዓተ ፡
ሌሊት ፡ ሁሉ ፡ ይጨልማል ፤
ወይሠርቅ ፡ በይእቲ ፡ ዕለት ፡ ሳብዓየ
እደ ፡ ጥንቁቀ ፤
በዚያች ፡ ቀን ፡ ጠንቅቆ ፡ ቈጥሮ ፡
፯ ክፍለ ፡ ብርሃን ፡ ተቀብሎ ፡
ሠርቅ ፡ ያደርጋል ፤

፲፬ ፤ ወይወፅእ ፡ ወይጸንን ፡ እም
ሥራቀ ፡ ፀሐይ ፤
ከፀሐይ ፡ መውጫ፤ ከምሥራቅ ፡
ይርቃል ፤ አንድም ፡ ፀሐይ ፡
ወደ ፡ ምሥራቅ ይቀርባል ፤
ወያበርህ ፡ በተረፈ ፡ ዕለቱ ፡
፯ተ ፡ ወ፯ተ ፡ እደ ፡
ሠርቅ ፡ አድርጎ ፡ በተረፈው ፡
ቀን ፡ ፯ት፡ ፯ት ፡ ክፍለ ፡ ብር
ሃን ፡ እየተቀበለ ፡ ያበራል።

## ምዕራፍ ፡ ፸፪

፩ ፤ ወካልአ ፡ ምሕዋረ ፡ ወትእዛዘ ፡
ርኢኩ ፡ ሎቱ ፡ እንተ ፡ በውእቱ ፡ ትእ
ዛዝ ፡ ይገብር ፡ ምሕዋሮ ፡ ዘአውራኅ፤
በሕፀፁ ፡ አምሳል ፡ የሚያደርገ
ውን ፡ የምልአቱን ፤ በመንፈቁ፡
አምሳል ፡ የሚያደርገውን ፡ ሥር
ዓት ፤ የሚያደርገውን ፡ ሁለተኛ፡
መሄጃውን ፡ ሁለተኛ ፡ ትእዛዙን፡
አየሁለት ፤
፪ ፤ ወኵሎ ፡ አርአየኒ ፡ ዑርኤል ፡
መልአክ ፡ ቅዱስ ፤
ንጹሕ ፡ ክቡር ፡ የሚሆን፤
ዘውእቱ ፡ መራሒሆሙ ፡ ለኵሎሙ ፤
ይኸውም ፡ የሁሉ ፡ መጋቢያ
ቸው ፡ (መሪያቸው) ፡ የሚሆን ፡
ዑራኤል ፡ ሁሉን ፡ አሳየኝ ፤
፫ ፤ ወምንባሪሆሙ ፡ ጸሐፍኩ ፡
በከመ ፡ አርአየኒ ፤

ሠረገላቸውን ፣ አነዋወራቸውን፤ ሥርዓታቸውን ፡ እንዳሳየኝ ፡ ጻፍኩ ፤

፬ ፤ ወጸሐፍኩ ፡ አውራኂሆሙ ፡ በከመ ፡ ሀለዉ ፤
ምግብናቸውን ፣
ወርእየተ፡ ብርሃኖሙ፡
መልክአ ፡ ብርሃኖሙ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ የብርሃናቸውን፡ መልክ ፡ ጻፍኩ ፤

፭ ፤ እስከ ፡ ተፈጸመ ፡ ፲ቱ ወ፭ቱ ፡ መዋዕል ፤
አሥራ ፡ አምስት ፡ ቀን ፡ እስኪ ፈጸም ፡ ድረስ ፡የብርሃናቸውን ፡ መልክ ፡ አየሁ ፣ ፲ት ፡ ፲ት ፡ ክፍለ ፡ ብርሃን ፡ እየተጨመረለት ፡ እስከ ፡ አስራ ፡ አምስት ፡ ቀን ፡ ይመላልና ፤
በ፩ዱ፡ ፲ተ ፡ ፲ተ ፡ እደ ፡ ይፌጽም ፡ ኵሉ ፡ ብርሃኖ ፡ በምሥራቅ ፣ ወበበ፲ቱ፡ ፲ቱ ፡ እደ ፡ ይፌጽም ፡ ኵሉ ፡ ጽልመቶ ፡ በምዕራብ ፣
ብርሃኖ ፡ በምዕራብ ፡ ጽልመቶ በምሥራቅ ፡ ሲል ፡ ነው ፣ ፲ት ፡ ፲ት ፡ ክፍለ ፡ ብርሃን ፡ እየተነሳው ፣ ብርሃኑን ፡ በምዕራብ ፡ ይጨርሳል ፤ ጨለማ ፡ ይሆናል ፤ ፲ት ፡ ፲ት፡ ክፍለ ፡ ብርሃን ፡ እየተጨመረለት ፡ ጨለማውን ፡ ይጨርሳል ፣ ብርሃን ፡ ይሆናል ፤ አንድም ፡ ንባቡ ፡ እንዳለ ፡ ፲ት ፡ ክፍለ ፡ ብርሃን ፡ እየተነሳው ፡ በምዕራብ ፡ ጨለማውን ፡ ይጨርሳል ፣ ጨለማ ፡ ይሆናል ፣ ፲ት ፡ ፲ት ፡ ክፍለ ፡ ብርሃን ፡ እየተጨመረለት ፣ በምሥራቅ ፡ ብርሃኑን ፡ ይጨርሳል ፤ ብርሃን ይሆናል ፤ አንድም ፡ በምዕራብ ፡ ሠሌዳው ፡ የተቀበለው ፡ ብርሃኑን፣ በምሥራቅ ፡ ሠሌዳው ፡ ያጣዋል፤

፮ ፤ ወበአውራኅ ፡ እሙራት ፡ ይዌ ልጥ ፡ ምዕራባቲሁ ፤
በታወቁ ፡ አውራኅ ፡ (ወራቶች) በመንፈቁ ፡ መግቢያውን ፡ ይለ ውጣል ፣ በሕፀፁ ፡ ፳፰ ቀን ፡ አብርቶ ፣ በ፳፱ኛው ፡ ጠፍ ፡ አድሮ ፣ በ፴ ፡ ሠርቅ ፡ ያደርጋ ልና ፤
ወበአውራኅ ፡ እሙራት ፡ የሐውር ፡ ምሕዋሪሁ ፡ ፩ደ ፡ ፩ደ ፣
በታወቁ፡ አውራኅ ፡ በመንፈቁ ፡ አንድ ፡ አንድ፡ ቀን ፡ እያተረፈ፡ መንገዱን፡ ይሄዳል ፤ በምላት ፡ ፳፱ ፡ አብርቶ ፣ በ፴ ጠፍ ፡ አድሮ ፣ በ፴፩ኛው ፡ ሠርቅ ፡ ያደርጋልና ፤ አንድም ፡ ወበአ ውራኅ ፡ እሙራት ፡ በታወቁ ፡ አውራኅ ፡ (ወራቶች) ፡ በመን ፈቁ፡ መግቢያውን፡ ይለውጣል ፣ በምልዓቱ ፡ እስከ ፡ ፲፭ ፡ ቀን ፡ ብርሃን፡ እየተጨመረለት ፣ እስከ፡ ፲፬ ፡ ቀን ፡ እየተነሳው ፣ ፳፱

ቀን ፡ አብርቶ ፤ በ፴ኛው ፡ ቀን ፡
ጠፍ ፡ አድሮ ፤ በ፴፩ኛው ፡ ቀን
ሠርቅ ፡ ያደርጋልና ፤
ወበአውራኅ ፡ እሙራት ፡ የሐውር ፡
ምሕዋሪሁ ፡ አሐደ ፡ አሐደ ፤
በታወቁ ፡ አውራኅ ፡ (ወራቶች) ፡
በመንፈቁ ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡
እያጐደለ ፤ በሕፀፁ ፡ እስከ ፡ ፲፬፡
ቀን ፡ ብርሃን ፡ እየተጨመረለት ፤
እስከ ፲፬ ፡ ቀን ፡ እየተነሣው ፤
፳፰ ፡ ቀን ፡ አብርቶ ፡ በ፳፱ ፡
ቀን ፡ ጠፍ ፡ አድሮ ፤ በ፴ኛው ፡
ቀን ፡ ሠርቅ ፡ ያደርጋልና ፤
፮ ፤ በክልኤቱ ፡ ወርኀ ፤
በ፮ኛው ፡ ወር ፤ በ፳፱ነኛውና ፡
በ፴ኛው ፡ ቀን ፤
የዐርብ ፡ ምስለ ፡ ፀሐይ ፤
ጨረቃ ፡ ከፀሐይ ፡ ጋራ ፡ ይገባል ፤
በእሉ ፡ ፪ቱ ፡ ኀዋኅው ፡ እለ ፡ በማ
ዕከል ፤
በመካከል ፡ ባሉ ፡ በእሊህ ፡ በ፪ቱ ፡
ኀዋኅው ፡ በመጋቢትና ፡ በሚያ
ዝያ ፡ ኀዋኅው ፤ ማዕከል ፡ አላ
ቸው ፤ በቀኝ ፡ የግንቦት ፤ የሰኔ ፤
በግራ ፡ የጥር ፤ የየካቲት ፡
አሉና ፤
በሣልስ ፡ ወበራብዕ ፡ ኖኅት ፤
ዘውእቶሙ ፡ ሣልስ ፡ ወራብዕ ፡
ሲል ፡ ነው ፤ እሊህም ፡ የመ
ጋቢት ፡ የሚያዝያ ፡ ናቸው ፤

ይወፅእ ፡ ሰቡዐ ፡ መዋዕለ ፤
በአንድ ፡ ኖኅት ፡ (መስኮት) ፫
ቀን ፤ በአንድ ፡ ኖኅት ፡ ፬ ቀን ፡
ይወጣል ፤
፳ ፤ ወየዓውድ ፡ ወይገብዕ ፡ ካዕበ ፡
በኖኅት ፡ እንተ ፡ ይወጽእ ፡ ፀሐይ ፤
ዳግመኛም ፡ ዙሮ ፡ ተመልሶ ፡
ፀሐይ ፡ በሚወጣበት ፡ መስኮት
ይወጣል ፤
ወበውእቱ ፡ ይፌጽም ፡ ኵሉ ፡ ብርሃኖ ፤
በዚያም ፡ መስኮት ፡ ብርሃኑን ፡
ሁሉ ፡ ይቀበላል ፤ አንድም ፡
ብርሃኑን ፡ ያጣል ፤
፱ ፤ ወይጸንን ፡ እምፀሐይ ፤
ከፀሐይ ፡ ይርቃል ፤ አንድም ፡
ወደ ፡ ፀሐይ ፡ ይቀርባል ፤
ወይበውእ ፡ ሰሙነ ፡ መዋዕለ ፡ በሳ
ድስት ፡ ኖኅት ፡ እንተ ፡ እምኔሃ ፡
ይወፅእ ፡ ፀሐይ ፤
ፀሐይ ፡ በሚወጣበት ፡ በ፮ኛው
በሰኔ ፡ ኖኅት ፡ ፰ ቀን ፡ ይገባል ፤
፲ ፤ ወሶበ ፡ ይወፅእ ፡ ፀሐይ ፡ እም
ራብዕት ፡ ኖኅት ፡ ይወፅእ ፡ ሰቡዐ ፡
መዋዕለ ፤
ፀሐይም ፡ ካራተኛዪቱ ፡ መስኮት
በወጣ ፡ ጊዜ ፡ በሚያዝያው ፡
ኖኅት ፡ ፮ ቀን ፡ ይወጣል ፤
እስከ ፡ ይወፅእ ፡ እምነ ፡ ሐምስት ፤
ከአምስተኛዪቱ ፡ መስኮት ፡ ከአም
ስተኛዪቱ ፡ ወር ፡ ከግንቦቱ ፡
ኖኅት ፡ እስኪወጣ ፡ ድረስ ፤

፲፩ ፤ ወካዕበ ፡ ይገብእ ፡ ሰቡዐ ፡ መዋዕለ ፡ በኆኅት ፡ ራብዒት ፤
ዳግመኛም ፡ ተመልሶ ፡ በአራተ ኛዪቱ ፡ መስኮት ፡ ሰባት ፡ ቀን ይወጣል ፤
ወይፌጽም ፡ ኵሎ ፡ ብርሃኖ ፤
ብርሃኑንም ፡ ሁሉ ፡ ይቀበላል ፤ አንድም ፡ ብርሃኑን ፡ ያጣል ፤
ወይጸንን ፡ ወይበውእ ፡ በቀዳሚት ፡ ኆኅት ፡ ሰሙነ ፡ መዋዕለ ፤
ይርቃል ፤ በመጀመሪያዪቱም ፡ መስኮት፡ ስምንት ፡ቀን፡ ይገባል፤
ወካዕበ ፡ ይገብእ ፡ ሰቡዐ መዋዕለ፡ በራብዕት ፡ ኆኅት ፡ እንተ፡ እምኔሃ ፡ ይወፅእ ፡ ፀሐይ ፤
ዳግመኛም ፡ ተመልሶ ፡ ፀሐይ ፡ ከእርሷ ፡ በሚወጣባት ፡ በሚያ ዝያ ፡ በአራተኛዪቱ ፡ መስኮት ፡ ፯ ቀን ፡ ይገባል ፤ አንድም ፡ በእሉ ፡ ፪ቱ ፡ ኀዋኀው ፤ በየካ ቲትና ፡ በግንቦት ፡ ኀዋኀው ፡ ይወጣል ፤ የየካቲትና ፡ የግንቦት፡ ማዕከል ፡ አላቸው ፤ የየካቲቱ ፡ በግራ ፤ የጥር ፡ በቀኝ ፤ የመጋ ቢት ፡ ለግንቦቱ ፡ በቀኝ ፤ የሰኔ ፡ በግራ ፤ የሚያዝያም ፡ አሉና ፤ በሣልስ ፤ ወበሣልስ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ በመጋቢትም ፤ ወበራብዕ ፡ በሚያዝያ ፡ ባራት ፡ ይወጣል ፤

ሰቡዐ ፡ መዋዕለ ፤ በ፫ኛው ፡ ኆኅት ፡ ሁለት ፡ ሁለት ፡ ቀን ፡ በአንዱ ፡ ኆኅት ፡ አንድ ፡ ቀን፤
ወሶበ ፡ ይወፅእ ፡ ፀሐይ ፡ እም ራብዒት ፡ ኆኅት ፤ እም፭ቱ ፡ ኀዋኀው ፡ ሲል ፡ ነው፤ ካ፭ቱ ፡ ኀዋኀው ፡ ይወጣል ፤ እስከ ፡ ይወጽእ፡እምሐምስት፤ከግንቦቱ ፡ ኆኅት ፡ እስኪወጣ ፡ ድረስ ፡ ደርሶ ፤ ወካዕበ ፡ ይገብእ ፡ በኆኅት ፡ ራብዕት ፡ በ፭ቱ ፡ ኀዋኀው ፡ ሲል ፡ ነው ፤ ካ፭ቱ ኀዋኀው ፡ ይወጣል ፤ በየካቲት ፤ በመጋቢት ፤ በሚያ ዝያ ፤ በግንቦት ፡ ኆኅት ፡ ፯ ቀን ፡ ይወጣል ፤ ወይበውእ ፡ በቀዳሚት፡ ኆኅት ፡ በጥር ፡ ኆኅት ፡ ይገባል ፤ ወካዕበ ፡ ይገብዕ ፡ ሰቡዐ ፡ በራብዕት ፡ በ፭ቱ ፡ ኀዋኀው ፡ ሲል ፡ ነው ፤ ባራቱ ፡ ኀዋኀው ፡ ይገባል፤ ፩ ፤ ፯ ፤ ቈጠረ ፤ ፳፰ ይሆናል፤ ፪ ፤ ፰ ፡ ቈጠረ ፤ ፲፯ ፡ ይሆናል ፤ ቢገጥሙት ፡ ፳፰ና ፡ ፲፯ት ፡ ፵፭ ፡ ይሆናል ፤ ፵ው ፡ የምሉን ፡ ተናገረ፤ ፲፭ ፡ ይተርፋል ፤ የሕፀ ፁን ፡ ተናገረ ፤ አንድም ፡ ፳፱ ፡ የሕፀፁን ፡ ተናገረ ፤ ፲፮ ፡ ይተ ርፋል ፤ የምሉውን ፡ በሄኖክ ፡

ተናገረ ፤ አንድም : ሄኖክስ : የተናገረው : ፱ ፯ : ፱ ፰ : ነው ፤ ያንኑ : መደጋገም : ነው : እንጂ ፤ ፰ና ፰ት : ፲፯ : ይሆናል ፤ ፯ና : ፯ ፲፬ ይሆናል ፤ ይህ : ፴ ነው : የምሉን : ተናገረ ፤ የሕፀፁንም: ይህን : ያህል : አለው ፤ ለሄኖክ : እኩሌታውን : በእኩሌታው : ማሳየት : ልማዱ : ነው ፤

፲፫ ፤ ወከመዝ : ርኢኩ : ምንባሮሙ : በከመ : ሥርዓተ : አውራኂሆሙ ፤

በየምግብናቸው : እንደሚሠሩት : ሥርዓት : እንደዚህ : አየሁ ፤

ይሠርቅ : ወየዓርብ : ፀሐይ ፤

ፀሐይ : ይወጣል ፤ ይገባል ፤

ጉባኤ

፲፬ ፤ ወበእማንቱ : መዋዕል : ይትዌሰክ : ፰ቱ : ዓመት ፤

ወበእማንቱ : ፰ ዓመት : ይትዌሰክ : መዋዕል : ሲል : ነው ፤ በሊህ : በ፰ቱ : ዘመን : ቀን : ይጨመራል ፤ ውስጥ : ለውስጥ : ዘመን : ሲቈጥር : መጥቶ : ነበርና : ከዚህ : ገለጸው ፤

ወይበጽሖ : ለፀሐይ : ፴ : መዋዕል፤

ከጨረቃ : ለፀሐይ : ከ፰ ዘመን ፴ ቀን : ይጨመርለታል፤ ፬ ጳጉሜንን : ትቶ ፤ ጨረቃ : ከዓመቱ : የምታበራው : ፫፻፶፬ ቀን : ብቻ : ነውና ፤ ስድስት : ቀን : ከፀሐይ ፡ የምታጐድለውን፤ የምታሳንሰውን : ቈጥሮ ፤ የ፰: ዘመን : ፴ : ቀን : ነው ፤ ለፀሐይ : የሚደርሰው : አለ ፤

፲፭ ፤ ወኵሉሙ : መዋዕላት : ይበጽሕም : ለአሐዱ : ዓመት : እምእልኩ : ፰ ዓመት ፤

ካ፰ቱ : ዓመት : ለአንዱም : ለአንዱም: ዓመት : የሚደርሰው ፤

ተመሊያሙ : ይከውኑ : ፫ተ : ፭ተ : ወ፰ ወረቡዕ : መዋዕለ፤

ኬክሮሱም፤ ካልዒቱም ፤ ሣልሲቱም : ተመላልተው : ለአንዱ : ዓመት : የሚደርሰው : ፫፻፷፬ : ቀን : ነው ፤

፲፮ ፤ ወይበጽሕ : ምብጻሒሆሙ : ለፀሐይ : ወለከዋክብት : ስሱ : መዋዕል ፤

ከጨረቃ : አትርፈው : ለፀሐይ ለከዋክብት : የሚደርሳቸው : ካመቱ : ፲ ቀን : ነው ፤

እም፰ቱ : ዓመታት : በበስሱ : ይበጽሖሙ : ሠላሳ : ዕለት ፤

ካምስት : ዓመት : ፲ ፤ ፲ እያለ : ፴ ቀን : ይደርሳቸዋል፤

፲፯ ፤ ወየሐጽጽ : ወርኅ : እምፀሐይ: ወእምከዋክብት : ፴ : መዋዕለ ፤

ከ፰ቱ : ዓመት : ጨረቃ : ፹ : ቀን : ይጎድላል ፡ የላይኛውን : ገለ ጸው ፡

፲፩ ፡ ወወርኅ : ያመጽኦሙ : ለዓመ ታት : ጥንቁቀ ፡

ጨረቃ : ዓመታትን : ጠንቅቆ : ቈጥሮ : ዘመናትን : ያመጣቸ ዋል ፡ የጠፋን : ቈጥሮ ፡ አን ድም : ተንባላት ፡ አይሁድ : የሚቈጥሩ : በጨረቃ : ነውና ፡

፲፪ ፡ ወኮሎሙ : በከመ : ምን ባሪሆሙ : ለዓለም ፡

ለዘለዓለም፡ እንደሚኖሩት : አነ ዋወር ፡

ኢይበድሩ : ወኢይዴኀሩ : አሐተ : ዕለተ ፡

ከ፫፻፷፬ ቀን : አንዲት : ቀን : አያጎድሉም ፡ አያተርፉምም ፡ የጳጉሜን : ፭ኛዪቱን፡ ስለምን : ተዋት : ቢሉ : ከሱባዔ : ትርፍ ከሆነች : ብሎ ፡

አላ : ይዌልጡ : ዓመተ : በጽድቅ : ጥንቁቀ : በበ፫፻ወ፷ ወረቡዐ: መዋዕለ፡ ፫፻፷፬ቱን : ቀን : አንድ : እያሉ : ጠንቅቆ : ቈጥሮ : በእውነት : ዘመንን : ይለውጣሉ : እንጂ ፡ በሄኖክ : አቈጣጠር : ዓመቱ : ሦስት : መቶ : ስድሳ : አራት ቀን : ነውና ፡

፲፫ ፡ ለ፫ቱ : ዓመት : መዋዕሊሁ : ፲፻ : ወ፺ : ወ፪ቱ ፡

የ፫ቱ : ዓመት : ቀኑ : ሺሕ : ከ፺፪ : ነው ፡

ወለ፭ቱ : ዓመት : መዋዕሊሁ : ፲ ወ፰፻ : ወ፳ : መዋዕል ፡

ያ፭ቱ : ዓመት : ቀን : ሺሕ : ከ፰፻፳ ፡ ቀን : ነው ፡

ከመ : ይኩን : ለ፰ : ዓመት : ፳፻ : ወ፱፻ ወ፲ቱ : ወ፪ቱ : መዋዕል ፡

የ፰ : ዓመት : ቀኑ : ፪ : ሺሕ : ፱፻፲፪ : ቀን : ይሆን : ዘንድ ፡ ይህ : ቁጥር : ጳጉሜንን : አግብቶ : ፯ተኛውን : ቀን : ትቶ : ነው ፡

፲፬ ፡ ለወርኅ : ለባሕቲቱ : ይበጽሕ : መዋዕሊሁ : ለ፫ቱ : ዓመት : ፲፻ ወ፷ : ወ፪ : መዋዕል ፡

ለጨረቃ : የ፫ቱ ዓመት : የሚደር ሰው : ሺሕ : ከ፷፪ : ቀን : ነው ፡ ፬ቱን : ጳጉሜን ፡ ፯ቱን : ቀን : ትቶ : ነው ፡

፲፭ ፡ ወለሐምስቱ : ዓመት : የሐጽጽ : ፶ : መዋዕለ ፡

ባ፭ቱ : ዘመን : ፶ : ቀን : ይጎ ድላል ፡

እስመ : ይትዌሰክ : በፀአቱ : ዲበ : ፳ ወ፪ቱ : መዋዕል ፡

፳ወ፪ቱ : ያለው : እንደ : ምል ክት : ያለ : ነው ፡ ከ፫ ዓመት : ወደ : ፭ : ዓመት : በወጣ : ጊዜ : ቀን ይጨምራልና ፡ አንድም : ዲበን : ለማውጣት : በ፫ቱ : ዓመት : ላይ : ቀን : ይጨመ ራልና : ፶ : ቀን : ይጎድላል ፡

፳፫ ፤ ወይከውን : ለ፭ቱ : ዓመት : ፲ ወ፯፻ : ወ፸ : መዋዕል ፤

ለጨረቃ : የሚደርሰው : የ፭ : ዓመት : ሺሕ : ፯፻ ከ፸ : ነው ፤

ከመ : ይኩን : ለወርኀ : ለ፰ : ዓመት : መዋዕሊሁ : ፳፻ : ወ፰፻፴ : ወ፪ቱ : መዋዕል ፤

ለጨረቃ : በ፰ ዓመት : የሚደር ሰው : ሁለት : ሺሕ : ስምንት መቶ : ሠላሳ : ሁለት : ቀን : ይሆን : ዘንድ ፤

፳፬ ፤ እስመ : ሕፀፁ : ለ፰ : ዓመት: መዋዕሊሁ : ፹ ፤

የ፰ቱ ዓመት : አጕዳደሉ : ፹ : ቀን : ነውና ፤

ወኵሎሙ : መዋዕል : ዘሐፀ : እም፰ ዓመት : ፹ ፤

ከ፰ቱ ዓመት : የጐደለው : ቀን: ፹ ነው ፤ ፩ቱን : ጳጕሜን ፤ ፯ቱን : ዕለት : ትቶ : ነው ፤ ስለምን : ዘመን : ቈጠረ : ቢሉ : ዘመን : ከተፈጠረበት : እስካሉ በት : ድረስ : ቈጥሮ : ማወቅ : ይገባል : ሲል : ነው ፤ ይኸውስ : ቢሆን : ከፍ : ብሎ : ፱ : ፲ ፤ ዝቅ : ብሎ : ፯ ፮ :ያላለ ፤ ፰ ብቻ : ቈጥሮ : የተወ : ስለምን : ነው : ቢሉ ፤ ሰውማ : ስለምን : ማለ ቱን : ይተዋል ? መንፈስ : ቅዱስ : እንዳመገበው : ተናግሯል ፤ አን ድም : ፫ና : ፭ት : ፰ ፤ ፰ና፰ ፤ ፲፮ ፤ ፲፮ና፤ ፲፮ : ፴፪ : ይሆናል፤ ይህ : የፀሐይ : ነው ፤ ለጨረ ቃም : ይህን : ያህል : አለው ፤ ይበጽሕም : ለአሐዱ : ዓመት : ያለውን : ጨምሮ : ፴፫ : ይሆናል፤ ጌታ : በዚህ : ዓለም : ሰው : ሆኖ ፤ ሥጋ : ለብሶ ፤ ፴፫ : ዓመት : የመኖሩ : አምሳል ፤ ይበጽሕም : ለ፩ዱ : ዓመት : ያልነው : ለፀሐይ : እንዳለው : ለጨረቃም : አለው ፤ ፴፬ : ይሆ ናል ፤ ጌታም : በዚህ : ዓለም : የኖረውን : ጠንቅቆ : ቢቈጥሩት ፴፬ : ይሆናልና ፤ በማሕፀነ : ማርያም : ፱ ወር ፤ ያስተማረ በት : ፴፫ : ዓመት : ከ፫ : ወር ፤ ፱ : ወርና : ፫ : ወር ፤ አንድ : ዓመት : ይሆናል ፤ ቢገናኝ : ፴፬ ዓመት ይሆናል ::

፳፭ ፤ ወይትፌጸም : ዓመት : በጽ ድቅ ፤

በእውነት : ጠንቅቆ : ቈጥሮ : ዘመን : ይፈጸማል ፤

በከመ : መንበረ : ዚአሆሙ፤

እንደ : ከዋክብት : እንደ : ጨረቃ : አነዋወር ፤

ወመንበረ : ፀሐይ ፤

እንደ : ፀሐይ : አነዋወር ፤

፳፮ ፤ እለ : ይሠርቁ : እምኒ : ኆኅት : እለ : እምኔሆሙ : ይሠርቅ ወየዐርብ : መዋዕለ : ፴ ፤

ፀሐይ : ከሚወጣባቸው : ከሚገ ባባቸው : ኆኅት : የሚወጡ : ብሎ : ለከዋክብት : ቀጸለ ::

# ምዕራፍ ፹፪

፭ ፤ ወመራሕያኒሆሙ ፡ ለአርእስተ ፡ አእላፍ ፤

የወር ፡ መጋቢዎችን ፡የሚመሩ ፡ የ፲፩ ፡ መጋቢዎች ፡ ከሚወጡ ባቸው ፡ ከሚገቡባቸው ፡ የሚ ወጡ ፡ አርእስት ፡ አላቸው ፤ የወር፡ መጋቢዎችን ፡ ስለመሩ፤ አንድም ፡ የሺሕ ፡ አለቆችን ፡ ስለ ፡ መሩ ፤ አንድም ፡ የሺሕ ፡ አለቆችን ፡ የሚመሩ ፡ የወር ፡ መጋቢዎች ከሚወጡባቸው፡ ከሚገቡባቸው ፡ የሚወጡ ፡ ከዋክብት ፡ እንደሚ ኖሩት ፡ አነዋወር ፡ ዘመን ፡ ይፈ ጸማል ፤

እለ ፡ ዲበ ፡ ኵሉ ፡ ፍጥረት ፤

በፍጥረታት፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ የተ ሾሙ ፤

ወዲበ ፡ ኵሉ ፡ ከዋክብት ፤

በከዋክብት ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ የተሾሙ ፤

፮ ፤ ወምስለ ፡ ፬ቱ ፡ እለ ፡ ይትዌስኩ ፤

ከወር ፡ መጋቢዎች ፡ የሚጨ መሩ ፤ ከ፲፩ ፡ መጋቢዎች ፡ ጋራ ፡ የሚወጡ ፤ የሚገቡ ፤ አንድም፡ ከ፲፩ዱ ፡ የሚጨመሩ ፤ ከ፬ት ፡ ጳጉሜን ፡ ከዋክብት ፡ ጋራ ፡ ከሚ ወጡባቸው ፡ ከሚገቡባቸው ፡ ኅዋኅው ፡ የሚወጡ ፡ (መስኮቶች)፡ የሚገቡ ፤

ወኢይትሌለዩ ፡ እምንባሮሙ ፤

ካነዋወራቸው ፡ የማይለዩ ፤

በከመ ፡ ኵሉ ፡ ሐሳበ ፡ ዓመት ፤

እንደ ፡ ዘመኑ ፡ ቁጥር ፡ የማይ ለዩ ፤

፯ ፤ ወእሉ ፡ ይትቀነዩ ፡ ፬ተ ፡ መዋ ዕለ ፤ እለ ፡ ኢይትሐሰቡ ፡ በሐሳበ ፡ ዓመት ፤

በዘመኑ ፡ ቍጥር ፡ የማይታሰቡ ፤ እነዚህ ፡ ኮከቦች ፡ አራቱን ፡ ጳጉሜን ፡ ይመግባሉ ፤

፰ ፤ ወበእንቲአሆሙ ፡ ይጌግዩ ፡ ቦሙ፡ ሰብእ ፤

በእነርሱ ፡ ሰዎች ፡ ይበድሉባቸ ዋል ፤

እስመ ፡ እሙንቱ ፡ ብርሃናት ፡ ይትቀነዩ ፤

እሊህ ፡ ብርሃናት ፡ ያበራሉና ፤

በጽድቅ ፡ በምንባረ ፡ ዓለም ፤

በዚህ ፡ ዓለም ፡ አነዋወር ፡ በእ ውነት ፡ ያበራሉና ፤ አንድም ፡ ወእሉ ፡ይትቀነዩ ፤ በ፬ቱ ፡ ጳጉ ሜን ፡ ያበራሉ ፤ እለ ፡ ኢይት ሐሰቡ ፡ በዘመን ፡ ቍጥር ፡ የማ ይቈጥሩ ፡ አይሁድ ፡ ተንባላት ፡ ጳጉሜን ፡ የለም ፡ ይላሉና ፤ ይጌ ግዩ ፡ የሉም ፡ ብለው ፡ አይሁድ ፤

ተንባላት ፡ ይበድላሉ ፤ እስመ ፡
እሙንቱ ፡ ብርሃናት ፡ ይትቀነዩ ፡
በጽድቅ ፡ በምንባረ ፡ ዓለም ፤
በዚህ ፡ ዓለም ፡ አነዋወር ፡ በእ
ውነት ፡ ያበራሉና ፡ ምንም ፡ ቢያ
በሩ ፡ ሰዎች ፡ የሉም ፡ ብለው ፡
ይበድላሉ ፤

፰ ፤ ፩ዱ ፡ በቀዳሚት ፡ ኖኀት ፤
አንዱ ፡ በመጀመሪያው ፡ መስኮት ፡
በጥቅምት ፤ በኅዳር ፤ በታኅሣሥ ፡
ኖኀት ፤

ወ፩ዱ ፡ በሣልስት ፡ ኖኀት ፤
አንዱ ፡ በሦስተኛው ፡ መስኮት ፡
በጥር ፤ በየካቲት ፤ በመጋቢት ፤

ወ፩ዱ ፡ በራብዕት ፡ ኖኀት ፤
አንዱ ፡ በአራተኛው ፡ መስኮት ፡
በሐምሌ ፡ በነሐሴ ፡ በመስከረም ፤

ወ፩ዱ ፡ በሣድስት ፡ ኖኀት ፤
አንዱ ፡ በስድስተኛው ፡ መስኮት ፡
በሚያዝያ ፡ በግንቦት ፡ በሰኔ ፡
ኖኀት ፡ (መስኮት) ፡ ይወጣል ፤

ወይትፌጸም ፡ ጥንቃቄ ፡ ዓለም ፤
ኍልቈ ፡ ዓለም ፡ ሲል ፡ ነው ፤ ይህ ፡
ዓለም ፡ ጸንቶ ፡ የሚኖርበትን ፡
ቀን ፡ ጠንቅቆ ፡ ቢቆጥሩት ፤

በበሠለስቱ ፡ ምእት ፡ ወስሳ ፡ ወረቡዕ
ምንባረ ፡ ዓለም ፤
ይህ ፡ ዓለም ፡ ጸንቶ ፡ በሚኖር
በት ፡ በ፫፻፷፬ ፡ ቀን ፡ አንድ ፡ እያሉ ፡
የዓለም ፡ ቁጥር ፡ ይፈጸማል ፤

፲ ፤ እስመ ፡ ለትእምርት ፤
ለጸጉሜን ፤
ወለአዝማን ፤
ለ፬ቱ ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፤
ወለዓመታት ፤
ለ፫፻፷፬ ፡ ቀን ፤
ወለመዋዕል ፡ አርአየኒ ፡ ዑርኤል ፡
መልአክ ፤
ለ፤ቱ ፡ ዕለታት ፡ ተሹሟልና ፡
መልአኩ ፡ ዑራኤል ፡ አሳየኝ ፤
አንድም ፡ በዚህ ፡ ሁሉ ፡ ኮከብ
ተሹሟልና ፡ ዑራኤል ፡ አሳየኝ ፤

ዘአንበሮ ፡ እግዚእ ፡ ስብሐት ፡ ዘለዓለም ፤
ዘሤሞ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ የክብር ፡
ባለቤት ፡ ጌታ ፡ የሾመው ፤

ዲበ ፡ ኵሉሙ ፡ ብርሃናተ ፡ ሰማይ ፤
በሰማይ ፡ ባሉ ፡ በፀሐይ ፡ በጨ
ረቃ ፡ ላይ ፡ የተሾመ ፤

፲፩ ፤ ወበዓለም ፡ ከመ ፡ ይምልኩ ፡
በገጸ ፡ ሰማይ ፤
በሰማይ ፤ በምድር ፤ ያበሩ ፡
ዘንድ ፤

ወይትረአዩ ፡ ዲበ ፡ ምድር ፤
ወደዚህ ፡ ዓለም ፡ ይመጡ ፡ ዘንድ ፡
በዚህ ፡ ዓለምም ፡ ይመግቡ ፡ ዘንድ ፤

፲፪ ፤ ወይኩኑ ፡ መራሕያነ ፡ ለመዓ
ልት ፡ ወለሌሊት ፡ ፀሐይ ፡ ወወርኅ ፡
ወከዋክብት ፤

ፀሐይ ፡ ጨረቃና ፡ ከዋክብት ፡ በመዓልትም ፡ በሌሊትም ፡ ይመ ግቡ ፡ ዘንድ ።

ወኮሎሙ ፡ ቅንየታት ።

በግብራቸው ፡ ቅኔየታት ፡ ብሏቸ ዋል ። አንድም ፡ ቅኑያን ፡ ሲል ። አንድም ፡ ቅንየታት ፡ የሚባሉ ፡ ከዋክብት ፡ እሉና ።

እለ ፡ የፀውዱ ፡ በኮሎሙ ፡ ሠረ ገላተ ፡ ሰማይ ።

በሰማይ ፡ ሠረገላ ፡ ሁሉ ፡ የሚ ዞሩ ። አንድም ፡ በክበበ ፡ ሠረገላ ፡ ዘፀሐይ ፡ በሰማይ ። በሰማይ ፡ ያለ ፡ በፀሐይ ፡ ሠረገላ ፡ ክበብ የተከፈቱ ።

፱ ። ከመዝ ፡ ፲ተ ፡ ወ፪ተ ፡ ኆኀወ ፡ ርኅዋተ ፡ አርአየኒ ፡ ዑርኤል ፡ በክበበ ሠረገላ ፡ ዘፀሐይ ፡ በሰማይ ።

በሰማይ ፡ ያለ ፡ ፀሐይ ፡ በሚመ ላለስባቸው ።

እለ ፡ እምኔሆሙ ፡ ይወጽኡ ፡ አገሪሃ ለፀሐይ ።

የፀሐይ ፡ እግሮቿ ፡ ከእነርሱ ፡ የሚወጡባቸው ፡ የተከፈቱ ፡ አሥራ ፡ ሁለት ፡ መስኮቶችን ፡ ዑራኤል ፡ እንዲህ ፡ አሳየኝ ። ከቀደመው ፡ አሁን ፡ ጉላ ፡ ጉላ እያደረገ ፡ ያነባል ፡ ያመጣል ።

፲ ። ወእምኔሆሙ ፡ ይወፅእ ፡ ሞቅ ፡ ዲበ ፡ ምድር ።

ከእነርሳቸውም ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ዋዕይ ፡ (ድርቅ) ፡ ይወጣል ።

ሶበ ፡ ይትረኀዉ ፡ በአዝማን ፡ እለ ፡ እሙራን ፡ ቦሙ ።

በታወቁባቸው ፡ ኀዋኀው ፡ በሚ መግቡበት ፡ ዘመን ፡ በተከፈቱ ጊዜ ፡ ድርቅ ፡ ይወጣል ።

፲፩ ። ወለነፋሳት ።

የነፋሳት ፡ ኀዋኀው ፡ በተከፈቱ ጊዜ ።

ወለመንፈስ ፡ ጠል ።

ጠልን ፡ የሚያመጡ ፡ የነፋስ ፡ ኀዋኀው ፡ በተከፈቱ ፡ ጊዜ ።

ሶበ ፡ ይትረኀዉ ፡ በእዝማን ፡ ርኀዋት ። በሚመግቡበት ፡ ዘመን ፡ በተከ ፈቱ ፡ ጊዜ ።

በሰማይ ፡ ዲበ ፡ አጽናፍ ፡ አሠርተ ፡ ወክልኤተ ፡ ኆኀወ ፡ ርኢኩ ፡ በሰማይ ፡ በአጽናፈ ፡ ምድር ።

በጽንፈ ፡ ዓለም ፡ ያሉ ፡ በሰማያት ፡ የተከፈቱ ፡ አሥራ ፡ ሁለት ፡ ኀዋኀውን ፡ አየሁ ።

እለ ፡ እምኔሆሙ ፡ ይወፅኡ ፡ ፀሐይ ወወርኅ ። ወከዋክብት ።

ከእነርሱ ። ፀሐይ ። ጨረቃ ፡ ከዋክብት ፡ የሚወጡበትን ፡ አየሁ ።

ወኵሎሙ ፡ ግብራተ ፡ ሰማይ ፤
በሰማይ ፡ ያሉ ፡ ፍጥረታት ፡ የሚ
ወጡበትን ፡ አየሁ ፤
እምነ ፡ ምሥራቅ ፡ ወእምነ ፡ ምዕራብ ፤
በምሥራቅ ፡ ወጥተው ፣ በምዕ
ራብ ፡ የሚገቡበትን ፡ ኀዋኀው ፡
አየሁ ፤

፲፪ ፤ ወመሳክው ፡ ርኅዋት ፡ ብዙ
ኃት ፡ እምየማነ ፡ ወእምጸጋሙ ፤
በሚያዝያ ፡ ኀዋኀው ፡ በቀኝ ፡
በግራ ፡ የተከፈቱ ፡ መስኮቶችን
አየሁ ፤

፲፫ ፤ ወአሐቲ ፡ መስኮት ፡ በዘመነ ፡
ዚአሃ ፡ ታመውቅ ፡ ሞቀ ፤
አንዲቱ ፡ መስኮት ፡ በምትመግ
ብበት ፡ (በዘመኗ) ፡ ሙቀትን ፡ ታስ
ገኛለች ፤
ዘከመ ፡ እልኩ ፡ ኀዋኀው ፡ እለ ፡ እም
ኔሆሙ ፡ ይወፅኡ ፡ ከዋክብት ፤
ከእነርሳቸው ፡ ከዋክብት ፡ እንደ
ሚወጡባቸው ፡ የሚያሞቁ ፤
በከመ ፡ አዘዞሙ ፡ ወእለ ፡ ቦሙ ፡
የዐርጉ ፡ በከመ ፡ ኍልቆሙ ፤
እግዚአብሔር ፡ እንዳዘዛቸው ፡
ኮከቦቹ ፡ ከእነርሳቸው ፡ እንደሚወ
ጡባቸው ፣ እንደነዚያ ፡ መስኮ
ቶች ፡ አንዲቱ ፡ መስኮት ፡ በዘ
መኗ ፡ ሙቀትን ፡ ታስገኛለች ፤

፲፬ ፤ ወርኢኩ ፡ ሠረገላተ ፡ በሰማይ ፤
በሰማይ ፡ ያሉ ፡ ሠረገላትን ፡
አየሁ ፤
እንዘ ፡ ይረውፁ ፡ በዓለም ፡ እመልዕ
ልቴሆሙ ፡ ወእመትሕቴሆሙ ፡ ለእ
ልኩ ፡ ኀዋኀው ፤
በፀሐይ ፡ ሠረገላ ፣ በበላያቸውም ፣
በበታቻቸውም ፡ ሲሮጡ ፡ በሰማይ ፡
ያሉ ፡ የከዋክብት ፡ ሠረገላትን ፡
አየሁ ፣ ለፀሐይ ፣ ለጨረቃ ፣
ከዋክብት ፡ ከላይ ፡ እንደጥላ ፣
ከታች ፡ እንደ ፡ ጫማ ፣ ከፊት ፡
እንደፊታውራሪ ፣ ከኋላ ፡ እንደ ፡
ደጀን ፡ ሁነው ፡ ይሄዳሉና ፣
እለ ፡ ቦሙ ፡ ይትመየጡ ከዋክብት ፡
እለ ፡ ኢየዓርቡ ፤
የሚመግቡ ፡ ከዋክብት ፡ የሚመ
ለሱባቸው ፣ ከምሥራቅ ፡ ወጥ
ተው ፡ ከምዕራብ ፡ ደርሰው ፡ የማ
ይገቡ ፡ አሉና ፤ አንድም ፡ ትኩሳን ፡
ከዋክብት ፡ አሉና ፤ አንድም ፡
ሕፀፅ ፡ የሌለባቸው ፡ ከዋክብት ፡
አሉና ፤

፲፭ ፤ ወ፩ዱ ፡ የዐዓብዮሙ ፡ ለኵ
ሎሙ ፤
ሁሉንም ፡ አንዱ ፡ ፀሐይ ፡ ይበ
ልጣቸዋል ፤
ወውእቱ ፡ የዐውድ ፡ ለኵሉ ዓለም ፤
እርሱም ፡ በ፩ቱ ፡ መዓዝነ ፡ ዓለም ፡
የሚዞር ፡ ፀሐይ ፡ ይበልጣቸዋል ።

# ምዕራፍ ፸፮

፩ ፤ ወበአጽናፈ ፡ ምድር ፡ ርኢኩ ፡ ዐሠርተ ፡ ወክልኤተ ፡ ኆዋኀወ ፡ ርኅዋተ ፡ ለኵሎሙ ፡ ነፋሳት ፡ እለ፡ እምኔሆሙ ፡ ይወፅኡ ፡ ነፋሳት ፤

እንደ ፡ አርእስት ፡ ተናግሮት ፡ ነበርና ፡ አመጣው ፤ ለነፋሶች ፡ ሁሉ ፡ መውጫ ፡ መግቢያ ፡ የሚሆኑ ፡ ነፋሶች ፡ ከእነርሱ ፡ የሚወጡባቸው ፤ የተከፈቱ ፡ አሥራ ፡ ሁለት ፡ መስኮቶችንም በምድር ፡ ዳርቻ ፡ አየሁ ፤

፪ ፤ ወይነፍሑ ፡ ዲበ ፡ ምድር ፤

በዚህም ፡ ዓለም ፡ ይነፍሳሉ ፡

ወ፫ቱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ርኅዋት ፡ በገጸ ሰማይ ፤

፫ቱ ፡ በምሥራቅ ፡ የተከፈቱ ፡ ናቸው ፤

ወሠለስቱ ፡ በምዕራብ ፤ ወሠለስቱ ፡ በየማነ ፡ ሰማይ ፤

ሦስቱ ፡ በምዕራብ ፤ ሦስቱ ፡ በሰሜን ፡ የተከፈቱ ፡ ናቸው ፡

ወሠለስቱ ፡ በጺጋም ፤

ሦስቱ በደቡብ ፡ የተከፈቱ ፡ ናቸው ፤

፫ ፤ ወ፫ቱ ፡ ቀዳምያት ፤

በመጀመሪያ ፡ ያየኋቸው ፡፫ቱ ፤

እለ ፡ መንገለ ፡ ጽባሕ ፤

በምሥራቅ ፡ በኩል ፡ ናቸው ፤

ወ፫ቱ ፡ እለ ፡ መንገለ ፡ መስዕ ፡

ሦስቱ ፡ በሰሜን ፡ በኩል ፡ ናቸው ፤

ወ፫ቱ ፡ በድኅር ፡ እለ ፡ በጺጋም ፡ እለ መንገለ ፡ አዜብ ፤

ወደ ፡ አዜብ ፡ በኩል ፡ የሚሆን በግራ ፡ ባለ ፡ በኋላ ፡ በደቡብ ፡ ናቸው ፤

ወ፫ቱ ፡ በዓረብ ፤

፫ቱ፡ በምዕራብ ፡ ናቸው ፤

፬ ፤ ወበ፬ቱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ይወፅኡ ፡ ነፋሳተ ፡ በረከት ፡ ወሰላም ፤

በእሊህ ፡ በ፬ቱ ፡ መስኮቶች ፡ የፍቅርና ፡ የበረከት ፡ ነፋሳት ፡ ይወጣሉ ፤

ወእምእልኩ ፡ ሰመንቱ ፡ ይወጽኡ ፡ ነፋሳተ ፡ መቅሠፍት ፤

ከነዚያም ፤ ከስምንቱ ፡ መስኮቶች ፡ መቅሠፍት ፡ የሚያመጡ ነፋሶች ፡ ይወጣሉ ፤

፭ ፤ ወሶበ ፡ ይትፌነዉ ፡ ይደመስስዋ ፡ ለኵላ ፡ ምድር ፤

ወደዚህም ፡ ዓለም ፡ በተላኩ ፡ ጊዜ ፡ ምድርን ፡ ሁሉ ፡ ያጠፏታል ፤

ወለማይ ፡ ዘዲቤሃ ፡

በውሃ ፡ ውስጥ ፡ ያሉ ፡ ፍጥረታትን ፡ ያጠፉ ፡ ዘንድ ፤

ወለኵሉሙ ፡ እለ ፡ የኀድሩ ፡ ዲቤሃ ፡
ወለኵሉ ፡ ዘሀሉ ፡ ውስተ ፡ ማይ ፡
ወዲበ ፡ የብስ ፤
በእርሷ ፡ ላይ ፡ የሚኖሩትንም ፡
ሁሉ ፡ በየብስና ፡ በውሃው ፡ ላይ ፡
ያለውንም ፡ ሁሉ ፡ ያጠፏቸዋል ፤
፯ ፤ ወይወፅእ ፡ ቀዳማይ ፡ ነፋስ ፡
እምእልኩ ፡ ኆዋኅው ፡ ዘስሙ ፡ ጽባ
ሐይ ፤
ስሙን ፡ ጽባሐይ ፡ ከሚሉት ፡
ኀዋኅው ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡
ባለው፡ በመጀመሪያው ፡ኖኅት ፤
በቀዳሚት ፡ ኖኅት ፡ እንተ ፡ መንገለ
ጽባሕ ፡ ዘታጸንን፡ ለአዜብ ፤
ለአዜብ ፡ በምትቀርብ ፡ በመጀ
መሪያዪቱ ፡ መስኮት ፤
ይወፅእ ፡ እምኔሃ ፡ ድምሳሴ ፤
ከእርሷ ፡ ይህን ፡ ዓለም ፡ የሚያ
ጠፋ ፡ ጥፋት ፡ ይወጣል ፤
የብስ ፣ ወሞቅ ፣ ወኀጕል ፡
ድርቅ ፣ ጥፋት ፡ ይወጣል ፤
፰ ፤ ወበካልእት ፡ ኖኅት ፡ ማእከላ
ዊት ፡ ይወፅእ ፡ ርትዕ ፤
በመካከል ፡ ባለች ፡ በሁለተኛዪ
ቱም ፡ መስኮት ፡ ቅንነት ፡ ይወ
ጣል ፡
ወይወፅእ ፡ እምኔሃ ፡ ዝናም ፡ ወፍሬ ፣
ከእርሷም ፡ በጎ ፡ ዝናም ፡ በጎ ፡
ፍሬ ፤
ወሰላም ፣ ወጠል ፤
በጎ ፡ ፍቅር ፣ በጎ ፡ ልምላሜ ፡
ይወጣል ፤

፱ ፤ ወበሣልስት ፡ ኖኅት ፡ እንተ ፡
መንገለ ፡ መስዕ ፡ ይወፅእ ፡ ቊር ፡
ወየብስ ፤
በመስዕ ፡ በኩል ፡ ባለች ፡ በሦስ
ተኛዪቱም ፡ መስኮት ፡ ውርጭ
ድርቅ ፡ ይወጣል ፤
ወእምድኅረ ፡ እሉ ፡ ነፋሳት ፡
ዘመንገለ ፡ አዜብ ፡ ይወፅኡ ፡ በ፫ቱ ፡
ኆኅዋት ፡ ቀዳምያት ፤
በአዜብ ፡ በኩል ፡ ያሉ ፡ እነዚ
ህን ፡ ነፋሶች ፡ ካየሁ ፡ በኋላ ፡ በመ
ጀመርያ ፡ ባየኋቸው ፡ በ፫ቱ ፡ መስ
ኮቶች፡ ነፋሶች ፡ ይወጣሉ ፤
፲ ፤ በቀዳሚት ፡ ኖኅት ፡ እምኔሆን ፡
እንተ ፡ትጸንን ፡ ለመንገለ ፡ ምሥራቅ ፣
በ፫ቱ ፡ ኆዋኅው ፡ የሚወጡ ፡
ነፋሳትን ፡ ካየሁ ፡ በኋላ ፡ ወደ
አዜብ ፡ ካሉት ፡ ከ፫ቱ ፡ ኆዋ
ኅው ፡ ወደምሥራቅ ፡ ባለችው
በመጀመሪያዪቱ ፡ ኖኅት ፤
ይወፅእ ፡ ነፋስ ፡ ሞቅ ፡ ውዑይ ፣
የድርቅ ፡ ውዑይ ፡ ነፋስ ፡ ይወ
ጣል ፤
፲፩ ፤ ወበኖኅት ፡ እንተ ፡ ኀቤሃ ፡
ማእከላዊት ፡ ይወፅእ ፡ እምኔሃ ፡
መዓዛ ፣ ሠናይ ፡ ወጠል ፡ ወዝናም ፡
ወሰላም ፣ ወሕይወት ፤
በእርሷ ፡ አጠገብ ፡ ባለች ፡ በመ
ካከለኛዪቱም ፡ መስኮት ፡ ከእርሷ
በጎ ፡ ሽቱ ፡ በጎ ፡ ጠል ፡ በጎ ፡

ዝናም ፣ ፍቅር ፡ ድኅነት ፡ ይወ
ጣል ፤
፲፩ ፤ ወበሣልስ ፡ ኆኅት ፡ እንተ ፡
መንገለ ፡ ምዕራብ ፡ ይወፅእ ፡ እምኔሃ ፡
ጠል ፡ ወዝናም ፤
በምዕራብ ፡ በኩል ፡ ባለች ፡ በሦስ
ተኛዪቱ ፡ መስኮት ፡ ከእርሷ ፡
ክፉ ፡ ጠል ፡ ክፉ ፡ ዝናም ፡ ይወ
ጣል ፤
ወአናኩዕ ፡ ወድምሳሴ ፤
ክፉ ፡ ኵብኵባ ፡ ጥፋት ፡ ይወ
ጣል ፤
፲፪ ፤ ወእምድኅረ ፡ እሉ ፡ ነፋሳት ፡
ዘመንገለ ፡ መስዕ ፡ ዘስሙ ፡ ባሕር ፡
እምሠለስቱ ፡ ሳብዓይ ፡ ኆኅት ፡
እንተ ፡ መንገለ ፡ ምሥራቅ ፤
ወእምድኅረ ፡ እሉ ፡ ነፋሳት ፡ እም
ሠለስቱ ፡ ሳብዓይ ፡ ኆኅት ፡ እንተ ፡
መንገለ ፡ መስዕ ፡ ዘስሙ ፡ ባሕ
ርይ ፡ እንተ ፡ መንገለ ፡ ምሥ
ራቅ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ በ፮ቱ ፡ ነዋ
ኀው ፡ የሚወጡ ፡ ነፋሳትን ፡
ካየሁ ፡ በኋላ ፡ ስሙን ፡ ባሕር ፡
የሚሉት ፡ መዓዝን ፡ አጠገቡ ፡
ባለ ፡ በመስዕ ፡ ካሉ ፡ ከ፫ቱ ፡
ነዋኀው ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡
ባለች ፡ ሰባተኛ ፡ በምትሆን ፡
ባንዲቱ ፡ ኆኅት ፤
ዘታጸንን ፡ መንገለ ፡ አዜብ ፡ ይወፅእ
እምኔሃ ፡ ጠል ፡ ወዝናም ፡ አናኩዕ ፡
ወድምሳሴ ፤

ጠል ፣ ዝናም ፣ ኵብኵባ ፡
ጥፋት ፡ ይወጣል ፣ ኆኅቲቱን ፡
ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ ያለች ፡ አላት ፣
ምሥራቅን ፡ ለአዜብ ፡ አቅራቢያ ፡
የምትሆን ፡ አላት ፣ ለስድስት ፡
ነዋኀው ፡ ይህችን ፡ ሳብዓይ ፡
ብሎ ፡ ቀጸለ ፤
፲፫ ፤ ወበማእከላዊት ፡ ኆኅት ፡ ርት
ዕት ፡ ይወፅእ ፡ እምኔሃ ፡ ጠል ፡
ወዝናም ፡ ወሕይወት ፡ ወሰላም ፤
በቀናች ፡ በመካከለኛዪቱም ፡ መስ
ኮት ፡ ከእርሷ ፡ በጎ ፡ ዝናም ፣
በጎ ፡ ጠል ፣ ድኅነት ፡ ፍቅርም ፡
ይወጣል ፤
፲፬ ፤ ወበሣልስ ፡ ኆኅት ፡ እንተ ፡
መንገለ ፡ ምዕራብ ፡ እንተ ፡ ታጸንን ፡
ለመንገለ ፡ መስዕ ፤
በመስዕ ፡ በኩል ፡ የምትሆን ፡
ወደምዕራብ ፡ አጠገብ ፡ የምት
ሆን ፡ በ፫ኛዪቱ ፡ ኆኅት ፤
ይወጽእ ፡ እምኔሃ ፡ ጊሜ ፡ ወአስ
ሐትያ ፡ ወሐመዳ ፡ ወዝናም ፡ ወጠል
ወአናኩዕ ፤
ከእርሷ ፡ ጉም ፣ ውርጭ ፣ ዋግ ፣
ክፉ ፡ ጠል ፣ ክፉ ፡ ዝናም ፡
ኵብኵባም ፡ ይወጣል ፤
፲፭ ፤ ወእምድኅረ ፡ እሉ ፡ ፬ቱ ፡ ነፋ
ሳት ፡ እለ ፡ መንገለ ፡ ምዕራብ ፡ በቀ
ዳሚት ፡ ኆኅት እንተ ፡ ታጸንን ፡
ለመንገለ ፡ መስዕ ፤

ወእምድኅረ ፡ እሉ ፡ ነፋሳት ፡ እለ ፡ መንገለ ፡ ምዕራብ ፡ ፬ቱ ፡ በቀዳሚት ፡ ኖኀት ፡ ሲል ፡ ነው ፤

እሊህን ፡ አራቱን ፡ ነፋሳት ፡ ካየሁ ፡ በኋላ ፡ ፬ኛ ፡ መዓዝን ፡ በሚሆን ፡ በምዕራብ ፡ ካሉ ፡ ኀዋኀው ፡ በመጀመሪያዪቱ ፡ ኖኀት ፡ በመስዕ ፡ በኩል ፡ በምትሆን ፤

እምኔሃ ፡ ይወፅእ ፡ ጠል ፡ ወዝናም ፡ ወአስሐትያ ፡ ወቍር ፡ ወሐመዳ ፡ ወደደክ ፤

ከእርሷ ፡ ክፉ ፡ ጠል ፤ ክፉ ፡ ዝናም ፤ የረጋው ፡ የተበተነው ፡ ውርጭ ፤ ዋግ ፤ ቀቅ ፡ ይወጣል ፤

፲፪ ፤ ወእምነ ፡ ኖኀት ፡ ማእከላይት ፡ ይወፅእ ፡ ጠል ፡ ወዝናም ፡ ሰላም ፡ ወበረከት ፤

ከመካከለኛዪቱም ፡ መስኮት ፡ በጎ ፡ ጠል ፤ በጎ ፡ ዝናም ፤ ፍቅር ፤ በረከትም ፡ ይወጣል ፤

፲፫ ፤ ወበደኃሪት ፡ ኖኀት ፡ እንተ ፡ መንገለ ፡ አዜብ ፡ ይወፅእ ፡ እምኔሃ ፡ የብስ ፤ ወድምሳሴ ፤ ዋዕይ ፤ ወኃጕል ፤

በአዜብ ፡ በኩል ፡ ባለች ፡ በኋለኛዪቱም ፡ መስኮት ፡ ከእርሷ ፡ ድርቅ ፡ ጥፋት ፡ ዋዕይ ፡ ይወጣል ፤

፲፬ ፤ ወተፈጸማ ፡ ፲ሩ ፡ ወ፪ቱ ፡ ኀዋኀው ፡ ዘ፬ቱ ፡ ኀዋኀወ ፡ ሰማይ ፤

በ፬ቱ ፡ መዓዝነ ፡ ሰማይ ፡ ያሉ ፲፪ቱ ፡ ኀዋኀው ፡ (መስኮቶች) ፡ ተፈጸሙ ፤

ወኵሎ ፡ ትእዛዞሙ ፤

የ፲፪ቱን ፡ ሁሉ ፡ ትእዛዛቸውን ፡

ወኵሎ ፡ መቅሠፍቶሙ ፤

የ፲፪ቱ ፡ ነፋሳት ፡ መቅሠፍታቸውን ፤

ወኵሎ ፡ ሰላሞሙ ፡ አርአይኩከ ፡ ወልድየ ፡ ማቱሳላ ፤

ልጄ ፡ ማቱሳላ ፡ የ፬ቱን ፡ ነፋሳት ፡ ምሕረታቸውን ፡ ሁሉ ፤ መቅሠፍታቸውንም ፡ ሁሉ ፤ ተድላ ፡ ደስታቸውንም ፡ ሁሉ ፤ አሳየሁህ ፡ አለ ፤

፲፱ ፤ ይጼውዕዎ ፡ ለነፋስ ፡ ቀዳማዊ ፡ ጽባሐዊ ፡ እስመ ፡ ቀዳማዊ ፡ ውእቱ ፤

መጀመሪያ ፡ የወጣ ፡ ነውና ፡ መጀመሪያ ፡ የወጣውን ፡ ነፋስ ፡ ስሙን ፡ ጽባሕዊ ፡ ይሉታል ፤

፳ ፤ ወይጼውዕዎ ፡ ለካልእ ፡ አዜብ፡ እስመ ፡ ልዑል ፡ ህየ ፡ ይወርድ ፡ ወፈድፋደ ፡ ህየ ፡ ይወርድ ቡሩክ ፡ ዘለዓለም ፤

ልዑል ፡ ብርሃን ፡ በዚያ ፡ ይወርዳልና ፤ አንድም ፡ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ በዚያ ፡ ይወርዳልና ፤ ደብረ ፡ ሲና ፡ ያለች ፡ በዚያ ፡ በኩል ፡ ናትና ፡ ለካልዕ አዜብ ፡ ውዑይ ፡ ነፋስ ፡ ይወርዳልና ፤ ይወርድ ፡ ቡሩክ ፡ ብርሃን ፤ አንድም ፡ ጌታ ፡ በዚያ ፡ ይወርዳልና ፤

፳፩ ። ወለነፋስ ፡ ዘእምዕራብ ፡ ስሙ፡ ንቱግ፣
ከምዕራብ ፡ የሚነፍሰውን ፡ ነፋስ ስሙን ፡ ሕፁፅ ፡ (የጉደለ) ፡ ይሉታል ፣ በሚወጣበት ፡ በመዓዝኑ ፡ ስም ፡ ጠርተውታል ፣ እንደ ፡ ደሴት ፡ ሰው ፣ ከጉና ፡ የወጣውን ፡ ላጉኒ ፡ ላጉኒም ፡ ይላል፣ ከጐንደር ፡ የወጣውን ፡ ጐንደሬ ፡ ጐንደሪም ፡ ይላል ፣ ከወደ ፡ ደንቢያ ፡ ሲነፍስ ፡ ደንቢ ፣ ከወደ ፡ ጽባሕ ፡ ሲነፍስ ፡ ጽባሒ ፡ እንዲሉት ።
እስመ ፡ በህየ ፡ የሐፅፁ ፡ ኵሉ ፡ ብርሃናተ ፡ ሰማይ ፡ ወይወርዱ ።
የሰማይ ፡ ብርሃኖች ፡ ሁሉ ፡ በዚያ ፡ ይጐድላሉና ፡ ወደዚያም ይገባሉና ።
፳፪ ። ወራብዕ ፡ ነፋስ ፡ ዘስሙ መስዕ ፡ ይትከፈል ፡ ሠለስተ ፡ ክፍለ ። ስሙ ፡ መስዕ ፡ የሚባል ፡ አራተኛውም ፡ ነፋስ ፡ ከሦስት ፡ ይከፈላል ።
ወ፩ዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ማኅደር ፡ ለሰብእ ።
ከሦስቱ ፡ አንዱ ፡ ለሰው ፡ ሕይወት ፡ ነው ።
ወካልእ ፡ ለአብሕርተ ፡ ማያት ፡ ወበቀላያት ፡ ወበዖም ፡ ወበአፍላግ ።
ሁለተኛውም፡ በውሃ ፡ ባሉ ፡ባሕሮች ፣ በጥልቆችም ፣ በዛፍም ፡ በወንዞችም ፡ ላሉ ፡ ፍጥረታት ፡ ሕይወት ፡ ነው ።
ወበጽልመት ፡ ወበጊሜ ፣
በጉም ፣ በጨለማ ፣ ለተፈጠሩ ፡ ፍጥረታት ፡ ሕይወት ፡ ነው ።
ወሣልስ ፡ ክፍል ፡ በገነተ ፡ ጽድቅ ፣
ሦስተኛውም ፡ ክፍል ፡ ክብር ፡ ባለበት ፡ በገነት ፡ ላሉ ፡ ጻድቃን ሕይወት ፡ ነው ። ጻድቃንስ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሕይወትነት ተመግበው ፡ ይኖራሉ ፡ እንጂ ፣ በነፋስ ፡ ሕይወትነት ፡ ተመግበው ፡ አይኖሩም ፡ ብሎ ፡ በገነት ፡ ላሉ ፡ ፍጥረታት ፡ ሕይወት ፡ ነው፡ አለ ፣ ዕፀው ፡ አዕዋፍ ፡ አሉና ።
፳፫ ። ወሰብዓተ ፡ አድባረ ፡ ነዊኃነ ፡ ርኢኩ ፡ እለ ፡ ይነውኅ ፡ እምኵሉ ፡ አድባር ፡ እለ ፡ ውስተ ፡ ምድር ።
በዚህ ፡ ዓለም ፡ ካሉ ፡ ተራሮች ሁሉ ፡ የሚበልጡ ፡ ሰባት ፡ ረጃጅሞች ፡ ተራሮችን ፡ አየሁ ።
፳፬ ። ወእምኔሆሙ ፡ ይወፅእ ፡ አስሐትያ ።
ከእነርሱም፥ ውርጭ ፡ ይወጣል ።
ወየኀልፍ ፡ ወየሐውር ፡ መዋዕል ፡ ወዘመን ፡ ወዓመት፣
ቀኑም ፣ ዘመኑም ፣ ዓመቱም ፣ እንዲህ ፡ እየሆነ ፡ ያልፋል ።
ወመዋዕል ፣ ሰባቱ ፡ ዕለታት ፡ (ሰባቱ ፡ ቀኖች) ፡ ወዘመን ፣ አራቱ ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ ሁሉ ።
ወዓመት ።
፫፻፷፬ ፡ ቀን ፡ እንዲህ ፡ እያለ ፡ ያልፋል ።

፸፭ ፤ ወ፯ተ ፡ አፍላገ ፡ ዲበ ፡ ምድር ፡ ርኢኩ ፡ ዓበይተ ፡ እምኵሎሙ ፡ አፍላግ ፤
ከፈሳሾች ፡ ሁሉ ፡ የሚበልጡ ፡ ሰባት ፡ ፈሳሾችን ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ አየሁ ፤

ወ፩ዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ይመጽእ ፡ እምዓረብ ፡ ወውስተ ፡ ባሕር ፡ ዓቢይ ይክዑ ፡ ማዮ ፤
ከእነርሳቸው ፡ ፩ዱ ፡ ከምዕራብ ፡ ነቅቶ ፡ በየብስ ፡ ሂዶ ፡ በውቅያኖስ ፡ ውሀን ፡ ያፈስሳል ፤

፸፮ ፤ ወእልክቱ ፡ ፪ቱ ፡ ይመጽኡ ፡ እመስዕ ፡ እስከ ፡ ባሕር ፡ ወይክዕዉ ማዮሙ ፡ በባሕረ ፡ ኤርትራ ፡ እምሥራቅ ፤
እነዚያ ፡ ሁለቱ ፡ ከመስዕ ፡ ነቅተው ፤ ከወደምሥራቅ ፡ በኤርትራ ፡ ባሕር ፡ ውሀቸውን ፡ ያፈስሳሉ ፤

፸፯ ፤ ወእለ ፡ ተርፉ ፡ ፬ቱ ፡ ይወፅኡ ፡ በገቦ ፡ መስዕ ፡ እስከ ፡ ባሕረ ፡ ዚአሆሙ ፡ ባሕረ ፡ ኤርትራ ፤
የቀሩትም ፡ አራቱ ፡ ከመስዕ ፡ ነቅተው ፡ የእነርሱ ፡ ባሕር ፡ እስከሚሆን ፡ እስከ ፡ ኤርትራ ፡ ባሕር ፡ ድረስ ፡ ሂደው ፡ በመስዕይ ፡ በኩል ፡ ይፈስሳሉ ፡፡

፸፰ ፤ ወ፪ቱ ፡ በባሕር ፡ ዓቢይ ፡ ይሰወጡ ፡ ወበህየ ፡ ይቤሉ ፡ መድበራ ፤
ሁሉቱ ፡ ፈሳሾች ፡ ሰፊ ፡ ወደ ፡ ሆነ ፡ ወደ ፡ ውቅያኖስ ፡ ይመለሳሉ ፤ ይመጽኡ ፡ እመስዕ ፡ ያለውን ፡ ደገመው ፤ አንዱ ፡ ከምዕራብ ፡ ነቅቶ ፡ በየብስ ፡ ሂዶ ፡ ውቅያኖስ ፡ ይገባል ፤ ሁለቱ ፡ ከመስዕ ነቅተው ፡ በኤርትራ ፡ አጠገብ ፡ ሂደው ፡ በምሥራቅ ፡ ውሀቸውን ፡ በውቅያኖስ ፡ ያፈስሳሉ ፤ አራቱ ፡ ከመስዕ ፡ ነቅተው ፡ በኤርትራ ፡ ላይ ፡ ሂደው ፡ ውቅያኖስ ፡ ያፈስሳሉ ፤ አንድም ፡ እሊህ ፡ ሁለቱና ፡ ፬ቱ ፡ ፯ቱ ፡ ከመስዕ ፡ ነቅተው ፡ በኤርትራ ፡ ላይ ፡ ሂደው ፡ ውሀቸውን ፡ ውቅያኖስ፡ ያፈስሳሉ ፤ ወበህየ ፡ ይቤሉ ፡ መድበራ ፡ ጉባዔ ፡ ይገብሩ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ በውቅያኖስ ፡ ይሰበሰባሉ ፤ አንድም ፡ ይቤሉ ፡ መድበራ ፡ አንጻረ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ የበቁ ፡ ጻድቃን ፡ ጽኑ ፡ በረሐ ፡ ነው ፡ ይላሉ ፤

፸፱ ፤ ሰቡዐ ፡ ደሰያተ ፡ ዓበይተ ፡ ርኢኩ ፡ በባሕር ፡ ወበምድር ፤
በባሕርና ፡ በየብስ ፡ ያሉ ፡ ፯ቱን ፡ ደሴት ፡ አየሁ ፤

፪ቱ ፡ በምድር ፤
ሁለቱ ፡ በየብስ ፡ ናቸው ፤ እንደ ዘጌ ፡ እንደ ፡ ቆራጣ ፤

ወ፭ቱ ፡ በባሕር ፡ ዓቢይ ፤
አምስቱ ፡ በባሕር ፡ ናቸው ፡ እንደናርጋ ፡ እንደ ፡ ምፅራሕ ፡፡

# ምዕራፍ ፸፪
## ጉባኤ

፩ ፤ አስማቲ ፡ ለፀሐይ ፡ ከመዝ ፤
የፀሐይ፡ስሞች፡እንዲህ፡ናቸው ፤
አሐዱ ፡ ኦርያሬስ ፤ ወካልኡ ፡ ቶማስስ ፤
አንዱ ፡ ኦርያሬስ ፡ይባላል ፤ ሁለተኛውም ፡ ቶማስስ ፡ ይባላል ፤

፪ ፤ ወለወርኅ ፡ አርባዕቱ ፡ አስማት፡ ቦቱ ፤ አሐዱ ፡ ስሙ ፡ አሶንያ ፤ ወካልኡ ፡ እብላ ፤ ወሣልሱ ፡ ብናሴ ፤ ወራብዑ ፡ ኤራዕ ፤
በየቋንቋው ፡ በብዙ ፡ ስም ፡ ይጠሩታል ፤ አንድም ፡ በአንዱ ፡ ቋንቋም ፡ በብዙ ፡ ስም ፡ ይጠሩታል ፤ አንዱ ፡ ስሙ ፡ አሶንያ ፡ ይባላል ፤ ሁለተኛውም ፡ እብላ ፤ ሦስተኛው ፡ ብናሴ ፡ አራተኛውም፡ ኤራዕ ፡ ይባላል ፤

፫ ፤ እሉ ፡ እሙንቱ ፡ ፪ቱ ፡ ብርሃናት ፡ ዓበይት ፡ ወክበቦሙ ፡ ከመ ፡ ክበበ ፡ ሰማይ ፡ ወአምጣኒሆሙ ፡ ለክልኤሆሙ ፡ ዕሩያን ፤
ስሌዳቸው ፡ (መጠናቸው) ፡ የተካከለ ፡ ነው ፤ ዘውግ ፡ ያለውን ዕሩያን ፡ ብሎ ፡ አመጣው ፤ ታላላቆች ፡ ብርሃኖች ፡ እነዚህ ፡ ፪ቱ ፡ ናቸው ፤ ክበባቸውም ፡ እንደ ፡ ሰማይ ፡ ክበብ ፡ ነው ፤

፬ ፤ በክበበ ፡ ፀሐይ ፡ ፳ቱ ፡ ክፍለ ፡ ብርሃን ፡ ዘይትዌሰክ ፡ ቦቱ ፡ እምወርኅ ፤
ከጨረቃ ፡ በልጦ ፡ ለፀሐይ ፡ ክበብ ፡ የሚጨመርለት ፡ ፳ት ፡ ክፍለ ፡ ብርሃን ፡ አለ ፤
ወበመሥፈርት ፡ ትትወደይ ፡ እስከ ፡ የኀልፍ ፡ ሳብዕ ፡ ክፍለ ፡ ፀሐይ ፤
የፀሐይ ፡ ሰባተኛው ፡ ክፍለ ፡ ብርሃን ፡ እስኪፈጽም ፡ ድረስ ፡ ፳ት ፡ ፳ት ፡ ክፍለ ፡ ብርሃን ፡ ይጨመርላታል ፤

፭ ፤ ወየዐርቡ ፡ ወይበውዑ ፡ ውስተ ፡ ኆኀወ ፡ ምዕራብ ፤
ነግህ ፡ ሠርቅ ፡ ሲያደርግ ፡ ጨረቃና ፡ ፀሐይ ፡ አንድነት ፡ ይገባሉ ፤
ወየዓውዱ ፡ እንተ ፡ መስዕ ፡ ወእንተ ኃዋኀወ ፡ ምሥራቅ ፡ ይወጽኡ ፡ ዲበ ገጸ ፡ ሰማይ ፤
ወደ ፡ መስዕም ፡ ይዞራሉ ፤ በሰማይ ፡ ሁነው ፡ እያበሩ ፡ በምሥራቅ ፡ መስኮት ፡ ይወጣሉ ፤

፮ ፤ ወሶበ ፡ ይትነሣእ ፡ ወርኅ ፤
ጨረቃ ፡ በወጣ ፤ አንድም ፡ ብርሃን ፡ በተሳለበት ፡ ጊዜ ፤

ያስተርኢ ፡ በሰማይ ፤
በሰማይ ፡ ይታያል ፤
ወመንፈቀ ፡ ሳብዕ ፡ እደ ፡ ብርሃን ፡
ይከውን ፡ ቦቱ ፤
ነገ ፡ በሚሳልበት ፡ (በሚቀበለው) ፡
እደ ፡ ብርሃን ፡ መጠን ፡ ፯ት ፡
ክፍለ ፡ ብርሃን ፡ ይሳልበታል ፤
፯ ፤ ወበዐሡር ፡ ወረቡዕ ፡ ይፌጽም ፡
ኵሉ ፡ ብርሃና ፤
እስከ ፡ ፲፬ ቀን ፡ ድረስ ፡ ብርሃ
ኑን ፡ ፈጽሞ ፡ ያገኛል ፤ (ይቀ
በላል ፤) አንድም ፡ እስከ ፡ ፲፬
ቀን ፡ ድረስ ፡ ብርሃኑን ፡ ያጣል ፡
በሕፀፁ ፡ ነው ፤
ወሠለስቱ ፡ ትሕምስተ ፡ ብርሃን ፡
ይትወደይ ፡ ውስቴታ ፤
ሦስት ፡ አምስት ፡ ክፍለ ፡ ብር
ሃንም ፡ ይጨመርላታል ፤
፰ ፤ እስከ ፡ ዐሥር ፡ ወሓምስ ፡
ይትፌጸም ፡ ብርሃኑ ፡ ዚአሁ ፡ ለትእ
ምርተ ፡ ዓመት ፤
በምሉ ፡ ነው ፡ እስከ ፡ ፲፭ ፡
ቀን ፡ ድረስ ፡ ብርሃኑን ፡ ያጣል፤
ኑሮት ፡ ያጣል ፡ ማለት ፡ አይ
ደለም ፤ ልክ ፡ ሆኖ ፡ ያድራል ፡
ሲል ፡ ነው ፤
ወይከውን ፡ ፫ተ ፡ ትሕምስተ ፤
ሦስት ፡ አምስት ፡ ክፍለ ፡ ብርሃን ፡
ይሆናል ፡ በምሉ ፡ ነው ፤

ወይከውን ፡ ወርኅ ፡ በመንፈቀ ፡
ሳብዕተ ፡ እድ ፤
ጨረቃ ፡ የፀሐይን ፡ ፯ኛውን ፡
እጅ ፡ ተቀብሎ ፡ የሚያበራ ፡
ይሆናል ፤
፱ ፤ ወበሕፀፀ ፡ ዚአሁ ፤
ጨረቃ ፡ ሕፀፅ ፡ በምታደርግበት
ጊዜ ፤
በቀዳሚት ፡ ዕለት ፡ የሐፅፅ ፡ ፲ተ ፡
ወ፬ተ ፡ እደ ፡ ብርሃነ ፡ ዚአሁ ፤
በመጀመሪያው ፡ ቀን ፡ ፲፬ኛውን
እጅ ፡ ክፍለ ፡ ብርሃን ፡ ያጣል ፤
ወበሳኒታ ፡ የሐፅፅ ፡ ዐሡርተ ፡ ወሠ
ለስተ ፡ እደ ፤
በሁለተኛዪቱም ፡ ቀን ፡ አሥራ
ሦስተኛዪቱን ፡ ክፍለ ፡ ብርሃን ፡
ያጣል ፤
፲ ፤ ወበሣልስ ፡ የሐፅፅ ፡ ዐሠርተ ፡
ወክልኤተ ፡ እደ ፤
በሦስተኛውም ፡ ቀን ፡ አሥራ፡
ሁለተኛውን ፡ እጅ ፡ ክፍለ ፡ ብር
ሃን ፡ ያጣል ፤
ወበራብዑ ፡ የሐፀፅ ፡ ዐሠርተ ፡
ወአሐደ ፡ ክፍለ ፤
ባራተኛውም ፡ ቀን ፡ አሥራ ፡
አንደኛውን ፡ ክፍል ፡ ያጣል ፤
፲፩ ፤ ወበሓምስ ፡ የሐፅፅ ፡ አሠርተ፡
ክፍለ ፤
ባምስተኛውም ፡ ቀን ፡ አሥረኛ
ውን ፡ ክፍል ፡ ያጣል ፤

ወበሳድስ: የሐፅፅ : ተሰዓተ : ክፍለ ፤
በስድስተኛውም : ቀን : ዘጠነኛ
ውን : ክፍል : ያጣል ፤

፲፪ ፤ ወበሳብዕ : የሐፅፅ : ስመንተ
ክፍለ ፤
በሰባተኛውም : ቀን : ስምንተኛ
ውን : ክፍል : ያጣል ፤
ወበሳምን: የሐፅፅ : ሰብዓተ : ክፍለ ፤
በስምንተኛውም : ቀን : ሰባተኛ
ውን : ክፍል : ያጣል ፤

፲፫ ፤ ወበታስዕ : የሐፅፅ : ስድስተ :
ክፍለ ፤
በዘጠነኛውም : ቀን : ስድስተኛ
ውን : ክፍል : ያጣል ፤
ወበዐሥር : የሐፅፅ :ሐምስተ :ክፍለ፤
ባሥረኛውም : ቀን : አምስተኛ
ውን : ክፍል : ያጣል፤

፲፬ ፤ ወበዐሥርቱ : ወአሐዱ : የሐ
ፅፅ : አርባዕተ : ክፍለ ፤
ባሥራ : አንደኛውም : ቀን :
አራተኛውን : እጅ : ያጣል ፤
ወበዐሥርቱ : ወክልኤቱ : የሐፅፅ :
ሠለስተ : ክፍለ ፤
በአሥራ : ሁለተኛውም : ቀን :
ሦስተኛውን : እጅ : ያጣል ፤

፲፭ ፤ ወበዐሥርቱ : ወሠለስቱ : የሐ
ፅፅ : ክልኤተ : ክፍለ ፤
በዐሥራ : ሦስተኛውም : ቀን :
ሁለተኛውን : እጅ : ያጣል ፤
ወበዐሥርቱ : ወአርባዕቱ : የሐፅፅ:
መንፈቀ : ሰብዓቱ : እድ ፤
በዐሥራ : አራተኛው : ቀን :
ትናንት : ያጣችውን : ክፍለ :
ብርሃን : ያህል : ይነሣታል ፤

፲፮ ፤ ወኵሉ : ብርሃኑ : በ፲ ወ፭ቱ :
ዕለት : ይትዌዳዕ : ዘተርፈ : እምኵሉ፤
በ፲፭ተኛው : ቀን : ከብርሃን :
የቀረ : ብርሃኑን : ሁሉ : ይጨ
ርሳል ፤ እንዲህ : ማለቱ : ኑሮት :
ያጣዋል : ማለት : አይደለም ፤
በክ : (ብላሽ) :ሁኖ: ያድራል : ሲል :
ነው ፤ እስከ :፲፬ :ቀን : ያገኘውንስ :
እስከ : ፲፬ ቀን : ያጠዋል ፤ እስከ :
፲፭ ቀንስ : ያገኘውን : እስከ :
፲፭ : ቀን : አያጣውም ? ቢሉ :
አዎን : አያጣውም ፤ ፲፭ኛው
ንስ : ተበዝብዛ : ትቀራለች ፤
አንድ : ስፍር : ዐሥር : ክንድ
ሰፍሮ : ዳግመኛ : ሲሰፍሩት :
እንዲጐድል ፤ አሥር : ላዳን :
ሠፍሮ : ዳግመኛ : ሲሠፍሩት :
እንዲጐድል ፤

፲፯ ፤ ወበአውራኅ : እሙራት ይከ
ውን : በበ፳ : ወተሱዑ : መዋዕል :
ለወርኅ ፤
በታወቁ : አውራኅ : (ወሮች) :
በመንፈቁ : ፳፱ : ፳፱ : ያበራል :
በምሉ : ነው ፤

ወቦ ፡ ጊዜ ፡ በበ፳ ፡ ወሰሙን ፤
በመንፈቁ ፡ ፲፬ ፡ ፲፭ ቀን ፡
ያበራል ፤ (ምላት ፡ የሚደረግ
በት ፡ ጊዜ ፡ አለ ፤)

፲፫ ፤ ወካልአተ ፡ ሥርዓተ ፡ አርአ
የኒ ፡ ኡርኤል ፡ መልአክ ፡ ሶበ ፡
ይትወደይ ፡ ብርሃን ፡ ውስተ ፡ ወርኅ ፤
ብርሃን ፡ በጨረቃ ፡ በሚሳልበት ፡
ጊዜ ፡ የሚደረገውን ፡ ሌላ ፡ ሥር
ዓት ፡ መልአኩ ፡ ኡራኤል ፡ አሳየኝ ፤

፲፬ ፤ ወእምኀበ ፡ ይትወደይ ፡ እም
ፀሐይ ፡ ኵሉ ፡ ዘመነ ፡ ዘተሐውር ፤
ጨረቃ ፡ በምላት ፡ ከሚያበራ ፡
ከፀሐይ ፡ ብርሃን ፡ ከመቀበሏ ፡
የተነሣ ፤

ወርኀ ፡ ብርሃነ ፡ ዚአሃ ፡ ትወዲ ፡
በቅድመ ፡ ፀሐይ ፤
ጨረቃ ፡ ስሌዳዋን ፡ ትገድባለች ፤
አንድም ፡ በብርሃነ ፡ ዚአሃ ፡ ቢል ፡
በምትመግብበት ፡ ጊዜ ፡ ትትወ
ደይ ፡ አጥብቀህ ፡ ነው ፡ ጨረቃ ፡
ትገደባለች ፤

ወእስከ ፡ ዐሥር ፡ ወራብዕ ፡ መዋዕል
ይትፌጸም ፡ ብርሃና ፡ ውስተ ፡ ሰማይ ፤
እስከ ፡ አሥራ ፡ አራተኛው ፡ ቀን ፡
ድረስ ፡ ብርሃኗን ፡ ጨርሳ ፡ ትቀ
በላለች ፤

፳ ፤ ወሶበ ፡ ይውዒ ፡ ኵሉ ፡ ይት
ፌጸም ፡ ብርሃና ፡ ውስተ ፡ ሰማይ ፤
መላው ፡ ስሌዳ ፡ በተቃጠለ ፡
ጊዜ ፡ በምላት ፡ ያበራል ፤

ወቀዳሚት ፡ ዕለት ፡ ሠርቀ ፡ ትሰ
መይ ፤
መጀመርያዪቱም ፡ ጨረቃ ፡
የተወለደችበት ፡ ቀን ፡ ትባላለች ፤
እስመ ፡ በይእቲ ፡ ዕለት ፡ ይትነሣእ ፡
ላዕሌሃ ፡ ብርሃን ፤
በዚያች ፡ ቀን ፡ በእርሷ ፡ ብርሃን ፡
ይሳልባታልና ፤

፳፩ ፤ ወይትፌጸም ፡ ጥንቁቀ ፡ በዕ
ለተ ፡ ይወርድ ፡ ፀሐይ ፡ ውስተ ፡
ዓረብ ፡ ወእምነ ፡ ምሥራቅ ፡ የዐርግ
በሌሊት ፤
ፀሐይ ፡ በምዕራብ ፡ በሚወርድ
በት ፡ ጊዜ ፡ ፈጽሞ ፡ ያበራል ፤
ፀሐይማ ፡ የማይወርድበት ፡ የማ
ይወጣበት ፡ አለ ? ጨረቃ ፡
በምላት ፡ በምታበራበት ፡ ጊዜ ፡
ፀሐይ ፡ በምዕራብ ፡ ስትገባ ፡
ጨረቃ ፡ በምሥራቅ ፡ ስትወጣ ፤
አንድም ፡ ፀሐይ ፡ በምሥራቅ ፡
ስትወጣ ፤ ጨረቃ ፡ በምዕራብ
ስትገባ ፡ ይተያያሉና ፤

፳፪ ፤ ወያበርህ ፡ ወርኅ ፡ በኵሉ ፡
ሌሊት ፡ እስከ ፡ ይሠርቅ ፡ ፀሐይ ፡
በቅድሜሁ ፤
ፀሐይ ፡ በፊቱ ፡ እስኪወጣ ፡ ድረሱ ፡
ጨረቃ ፡ መላ ፡ ሌሊቱን ፡ ያበራል ፤
ወይትረአይ ፡ ወርኅ ፡ በቅድመ ፡
ፀሐይ ፤

ጨረቃ : ከፀሐይ : ጋራ : ፊት ለፊት : ይተያያል ፤

፳፫ ፤ ወእምነበ : ይወፅእ : ብርሃኑ: ለወርኀ : እምሀየ ፤

ጨረቃ : ብርሃን : ከተሣለበት : ቀን : ጀምሮ ፤

ካዕበ : የሐፅፅ እስከ : ይትዌዳዕ : ኵሉ : ብርሃን ፤

ጨረቃ :መጀመሪያ : ብርሃን : ከተሣለበት : ከዚያ : ብርሃኑ : ያንሣል : (ይነሳዋል) ፣ በምዕራብ: ሰሌዳው : መጀመሪያ : የተቀበላትን : ከምዕራብ : ሰሌዳው : መነሣት : ይጀምራል ፤

፳፬ ፤ ወየኀልፍ : መዋዕለ : ወርኀ : ወይነብር : ክበቡ : በከ : ዘአልቦ : ብርሃን ፤

እንዲህ : እየሆነ : ጨረቃ : የሚያበራበት : ወራት : ያልፋል ፣ ሠሌዳውም : ብርሃን : የሌለው : ጠፍ : ይሆናል ፤

፳፭ ፤ ወሠለስተ : ወርኀ : ይገብር : ፴ መዋዕለ : ለዘመኑ : ዚአሁ ፤

ሦስት : ወር : ምላት : በሚደረግባት : ዘመን : በ፴ኛው : ቀን : ሕፀፅ: ያደርጋል ፤ ሕፀፁን : ጨምሮ : ቈጥሮ : ነው : በምሉ : ነው ፤

ወሠለስተ : ወርኀ : ይገብር : በበ፳ : ወ፱ቱ : መዋዕል ፤

ሦስቱንም : ወር : ሕፀፅ : በሚደረግባቸው : ወራቶች : በሀያ : ዘጠኝ : በሀያ : ዘጠኝ : ቀን : ሕፀፅ : ያደርጋል ፣ ይህም :ጠፉን: ጨምሮ : ነው : በሕፀፁ ፤

እለ : በሙ : ይገብር : ታሕፃጺተ : ዚአሁ ፣

በ፴ኛውና : በ፳፱ነኛው : ሕፀፅ : የምታደርግባቸው : ብሎ : ቀጸለ ፤

፳፮ ፤ በዘመን : ቀዳማዊ ፤

በዘመን : መፀው : ጥቅምት : ኅዳር : ታኅሣሥ ነው ፤

ወበኖኅት : ቀዳማዊ ፤

በመጀመሪያ : በጥር : ኖኅት ፤

በመዋዕል : ፻ወ፸ : ወ፯ቱ : ወበዘመነ ሙፃኡ : ሠለስተ : ወርኀ : ያስተርኢ ፤

በመቶ : ሰባ : ሰባት : ቀን : ፫ወር : ፴ : ፴ቀን : ይታያል ፣ ጠፉን : ጨምሮ : ነው ፤

ወ፫ተ : ወርኀ : ያስተርኢ : በ፳ወ፱ቱ መዋዕል ፤

፫ወር : በ፳፱ ፣ በ፳፱ : ቀን : ያበራል : በሕፀፁ : ነው ፤

፳፯ ፤ በሌሊት : ያስተርኢ : በበ፳ : ከመ : ብእሲ ፣ ወመዓልተ : ከመ : ሰማይ ፤

በኸያ : በኸያ : ሌሊት : ሰው : መስሎ : ይታያል ፣ ብርሃን : ሲነሳው : እጅ : እግር : ያለው : ሁኖ :እንደ : ሰው : ይታያልና፤ አንድም : ብእሲ : ማለት : ብሩህ:

ማለት ነው ። ብሩህ ፡ ሆኖ ፡ ይታያል ፤

እስመ ፡ ካልዕ ፡ ምንትኒ ፡ አልባቲ ፡ ዘእንበለ ፡ ብርሃን ፡ ዚአሃ ፤

ከብርሃን ፡ ፀሐይ ፡ በቀር ሌላ ፡ ብርሃን ፡ የላትምና ፤

፸፰ ፤ ወይእዜኒ ፡ ወልድየ ፡ ማቱሳላ ፡ አርአይኩከ ፡ ኵሎ ፤

አሁንም ፡ ልጄ ፡ ማቱሳላ ፡ ሁሉን ፡ አሳየሁህ ። አስተማርሁህ ፤

ወተፈጸመ ፡ ኵሉ ፡ ሥርዓተ ፡ ከዋክብተ ፡ ሰማይ ፤

መጻፉ ፡ ከሆነ ፡ በኋላ ነውና ፡ ሳይናገረው ፡ ተፈጸመ ፡ አለ ፤

፸፱ ፤ ወአርአየኒ ፡ ኵሎ፡ ሥርዓቶሙ ፡ ለእሉ ፡ እንተ ፡ በኵሉ ፡ መዋዕል ፡ ወበኵሉ ፡ ዘመን ፤

በየቀኑ ፡ ሁሉ ፡ በየዘመኑ ፡ ሁሉ ፡ የሚያደርጉት ፡ የከዋክብት ፡ ሥርዓታቸውን ፡ ሁሉ ፡ አሳየኝ ፤

ዘበኵሉ ፡ ሥልጣን ፤

በየምግብናቸው ፡ በየሹመታቸውም ፡ ሁሉ ፤

ወበኵሉ ፡ ዓመት ፡ ወበሙፃኡ ፡ ወበትእዛዙ ፡ ወበኵሉ ፡ ወርኅ ፡ ወበኵሉ ፡ ሰንበታት ፤

በያመቱም ፡ በመግቢያው ፡ በታዘዘበትም ፡ ሁሉ ፡ በየወሩም ፡ ሁሉ ፡ በየሱባዔውም ፡ ሁሉ ። የሚሆነውን ፡ የነዚህን ፡ ሥርዓት ፡ አሳየኝ ፤

፹ ፤ ወሕፀፀ ፡ ወርኅ ፡ ዘይትገበር ፡ በሳድስት ፡ ኆኅት ፤

በስኔ ፡ ኆኅት ፡ የሚደረገውን ፡ የጨረቃን ፡ ሕፀፅ ፡ አሳየኝ ፤

እስመ ፡ በዛቲ ፡ ኆኅት ፡ ሳድሲት ፡ ይትፌጸም ፡ ብርሃኑ ፡ ዚአሁ ፤

በዚህች ፡ በስድስተኛዪቱ ፡ መስኮት ፡ ብርሃኑ ፡ ጨርሶ ፡ ይጠፋልና ፤

፹፩ ፤ ወእምኔሁ ፡ ይከውን ፡ ርእሰ፡ ወርኅ ፤

በስኔው ፡ ኆኅት ፡ ሠርቅ ፡ ይሆናል ፤

ወታሕፃፂት ፡ ዘይትገበር ፡ በኆኅት ፡ ቀዳሚት ፡ በዘመኑ ፡ ዚአሁ ፤

ከዚያም ፡ በኋላ ፡ በጥር ፡ ኆኅት፡ የሚደረገውን ፡ ሕፀፅ ፡አሳየኝ ፤

፹፪ ፤ እስከ ፡ ይትፌጸም ፡ መዋዕል ፻ ወ፸ ወ፯ቱ ፡ በሥርዓተ ፡ ሰንበት ፡ ፳ወ ፭ቱ ፡ ወ፪ኤ ፡ መዋዕል ፤

በሱባዔ ፡ አቈጣጠር ፡ ኻያ ፡ አምስት ፡ ሱባዔ ፡ ከሁለት ፡ ቀን ፡ ነው ፡ መቶው ፡ ቀን ፡ ፲፬ ሱባኤ ፡ ሆኖ ፡ ፪ ቀን ፡ ይተርፋል ። ፸ው ፡ ቀን ፡ ፲ ሱባዔ ፡ ነው ፡ ፯ ፡ ቀን ፡ ፩ ሱባዔ ፡ ነው ። ቢገጥሙት ፡ ፳፭ ፡ ሱባዔ ፡ ሆኖ ፡ ፪ ቀን ፡ ይተርፋል ፡ የመንፈቁ ፡ ነው ፤

፴፫ ፤ ወዘየሐፅፅ ፡ እምፀሐይ ፡ ወሥርዓተ፡ ከዋክብት ፡ ሐሙስ ፡ መዋዕለ፤
ከፀሐይ ፡ ከከዋክብት ፡ ጨረቃ ፡ የምታንሰው ፡ ፭ ቀን ፡ ነው ፤ ፭ቱን ፡ ጳጕሜን ፡ ቈጥሮ ፡ ሕፀፁን ፡ ቈጥሮ ፡ ነው ፤ በሌላ ፡ ቤት፡ አቈጣጠር ፡ ግን ፡ የያዘው ፡ የመንፈቁን ፡ ነውና ፡ ፫ት ፡ ሕፀፅ ፡ ከ፩ቱ ፡ ጳጕሜን ፡ ሁለቱን ፡ ቢገጥሙት ፭ ነውና ፡ ይህ ፡ ነው፤
በዘመን ፡ ፩ዱ ፡ ጥንቁቀ ፤
አንዱን ፡ ዘመን ፡ ጠንቅቆ ፡ ቈጥሮ ፤
፴፬ ፤ ወሶበ ፡ ይትፌጸም ፡ ዝ መካን ፡ ዘትሬኢ ፤
ዘትሰምዕ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ የምትሰማው ፡ ይህ ፡ አንቀጽ ፡ በተፈጸመ ፡ ጊዜ ፤
ከመዝ ፡ አርአያ ፡ ወአምሳል ፡ እምኵሉ ፡ ብርሃን ፡ ዘአርአየኒ ፡ ዑርኤል ፡ መልአክ ፡ ዓቢይ ፤
ገናና ፡ መልአክ ፡ ዑራኤል ፡ ከብርሃኑ ፡ ሁሉ ፡ አንዱ ፡ ሳይቀር ፡ ያሳየኝ ፤ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ አምሳል፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ አለ ፤
በመንፈቁ ፡ አምሳል ፡ የመንፈቁ፤ በምሉ ፡ አምሳል ፡ የምሉ ፡ አለ ፤
ዘውእቱ ፡ መራሒሆሙ ፤
ይኸውም ፡ መሪያቸው ፡ መጋቢያቸው ፡ ነው፤

፴፭ ፤ ወበውእቱ ፡ መዋዕል ፡ አውሥአኒ ፡ ዑርኤል ፡ መልአክ ፡ ወይቤለኒ ፡ ነዋ ፡ አርአይኩከ ፡ ኵሎ ኦ ፡ ሄኖክ ፤
በዚያም ፡ ወራት ፡ መልአኩ ፡ ዑራኤል ፡ ሄኖክ ፡ ሆይ ፡ እነሆ ፡ ሁሉን፡ አሳየሁህ ፡ ብሎ ፡ መለሰልኝ ፤
፴፮ ፤ ወኵሎ ፡ ከሠትኩ ፡ ለከ ፡ ትርአዮ፡ ለዝ ፡ ፀሐይ ፡ወለዝ ፡ ወርኅ ፤
ይኸንን ፡ ፀሐይ ፡ ይኸንን ፡ ጨረቃ ፡ ታየው ፡ ዘንድ ፤
ወለእለ ፡ ይመርሕዎሙ ፡ ለከዋክብተ ሰማይ ፤
የወር ፡ መጋቢዎችን ፡ የሚመሩ ፡ የ፺፩ዱን ፤ የሺሕ ፡ አለቆችን ፡ የሚመሩ ፡ የወር ፡ መጋቢዎችን ፤ የዕለት ፡ መጋቢዎችን ፡ የሚመሩ ፡ የሺሕ ፡ አለቆችን ፡ ታያቸው ፡ ዘንድ ፡ ገለጽሁልህ ፤
፴፯ ፤ ወለኵሎሙ ፡ እለ ፡ ይመይጥዎሙ ፡ ግብሮሙ ፤
የዕለቱን ፤ የዕለቱ ፡ መጋቢ ፤ የሽሕውን ፡ የሺው ፡ መጋቢ ፤ የ፺፩ዱን ፤ የ፺፩ዱ ፡ መጋቢ ፡ ይለውጠዋልና ፤ ግብራቸውን ፡ የሚለውጡትን ፡ አሳየሁህ ፡ አለ ፤
ወአዝማኖሙ ፡ ወሙፃኢሆሙ ፤
የሚወጡበትን ፡ ዘመናቸውን ፤ መውጫ ፡ መግቢያቸውን ፡ የሚለውጡትን ፡ ታያቸው ፡ ዘንድ፡ ገለጽሁልህ ።

# ምዕራፍ ፳፯
## ጉባኤ

፩ ፤ ወበመዋዕለ ፡ ኀጥአን ፡ ክራማት ፡ የኀጽራ ፤
በኀጥአን ፡ ወራት ፡ የኃጥአን ፡ ኃጢአት ፡ በበዛበት ፡ ወራት ፡ ክራማት ፡ (ዘመኖች) ያጥራሉ ፤
በግንቦት ፡ በሰኔ ፡ የሚዘንመው በሐምሌ ፡በነሐሴ ፡ ይዘንማል ፤
ወዘርአ ፡ ዚአሆሙ ፡ ይከውን ፡ ደኃ ራዊ ፡ በምድሮሙ ፡ ወበሙፋሮሙ ፤
በሀገራቸው ፡ በመሰማሪያቸው ፡ ዘራቸው ፡ ወደኋላ ፡ ይሆናል ፤
በግንቦት ፡ በሰኔ ፡ የሚዘራው ፡ በሐምሌ ፡ በነሐሴ ፡ ይዘራል ፤
፪ ፤ ወኵሉ ፡ ግብር ፡ ዘዲበ ፡ ምድር ይትመየየጥ ፤
በዚህ ፡ ዓለም ፡ ያለው ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ይለዋወጣል ፤
ወኢያስተርኢ ፡ በዘመኑ ፤
በግንቦት ፤ በሰኔ ፡ የሚበቅለው ፡ በሰኔ ፡ በግንቦት ፡ በቅሎ ፤ በሐ ምሌ ፤ በነሐሴ ፡ የሚበቅለው ፡ በሐምሌ ፡ በነሐሴ ፡ በቅሎ ፡ አይታይም ፤
ወዝናም ፡ ይትከላአ ፡ ወሰማይ ፡ ታቀውም ፤
ሰማይ ፡ ዝናም ፡ ለዘር ፡ ጠል ፡ ለመከር ፡ ከመስጠት ፡ ትከለከ ላለች ፡ ትገታለች ፤

፫ ፤ ወበውእቱ ፡ አዝማን ፡ ፍሬ ፡ ምድር ፡ ይከውን ፡ ደኃራዊ ፤
በነሐሴ ፤ በመስከረም ፡ የሚደር ሰው ፡ በጥቅምት ፤ በኅዳር ፡ ይደ ርሳል ፤
ወኢይበቍል ፡ በዘመኑ ፡ ወፍሬ ፡ ዕፅ ይትከላዕ ፡ በዘመነ ፡ ዚአሁ ፤
በዘመኑም ፡ አይበቅልም ፡ የእን ጨቱም ፡ ፍሬ ፡ ከማፍራት ፡ ይከ ለከላል ፤
፬ ፤ ወወርኀ ፡ ይዌልጥ ፡ ሥርዓቶ፤
ጨረቃም ፡ ሥርዓቱን ፡ ይለው ጣል ፤
ወኢይትረአይ ፡ በዘመነ ፡ ዚአሁ ፤
በክረምት ፡ በደመና ፡ ተሸፍኖ ፡ ሲያበራ ፡ አይታይም ፤
፭ ፤ ወበእማንቱ ፡ መዋዕል ፡ ይትረ አይ ፡ ሰማይ ፤
በዚያ ፡ ወራት ፡ ሰማይ ፡ ጠርቶ ፡ ይታያል ፤ የደመና ፡ ምልክት ፡ አይታይበትም ፤
ወይበጽሕ ፡ አባር ፡ በጽንፈ ፡ ሠረገ ላት ፡ ዓቢይ ፡ በምዕራብ ፤
በምዕራብ ፡ በኩል ፡ ባለ ፡ በጽንፈ ፡ ሠረገላ ፡ ድርቅ ፡ ይመጣል ፤

ወይበርህ ፡ ፈድፋደ ፡ እምሥርዓተ ፡ ብርሃን ።

ከበጋው ፡ ሥርዓት ፡ ይልቅ ፡ በክረምት ፡ ያበራል ።

፮ ። ወይስሕቱ ፡ ብዙኃን ፡ አርእስቲሆሙ ፡ ለከዋክብተ ፡ ትእዛዝ ።

ወይዌልጡ ፡ ሲል ፡ ነው ። የወር ፡ መጋቢዎችን ፡ የሚመሩ ፡ የዘጠና ፡ አንድ ፤ የሽሕ ፡ አለቆችን ፡ የሚመሩ ፡ የወር ፡ መጋቢዎች ። የዕለት ፡ መጋቢዎችን ፡ የሚመሩ፡ የሽሕ ፡ አለቆች ፡ ሥርዓታቸውን ፡ ይለውጣሉ ። አንድም ፡ ሌሎች ፡ ከዋክብትን ፡ የሚመሩ ፡ የዕለት ፡ መጋቢዎች ፡ ሥርዓታቸውን ፡ ይለውጣሉ ።

ወእሉ ፡ ይመይጡ ፡ ፍናዊሆሙ ፡ ወግብሮሙ ።

ከዋክብት፡ ሥርዓታቸውን ፡ ይለውጣሉ፤ ሰዎች ፡ ይህን፡ ሁሉ ፡ መከራ ፡ (ምልክት) ፡ እያዩ ፡ ከኀጢአት ፤ ወደ ፡ ጽድቅ ፤ ከክህደት ፤ ወደ ፡ ሃይማኖት ፡ ይመለሳሉና ።

ወኢይትረአዩ ፡ በአዝማኒ ፡ ዚአሆሙ፡ እለ ፡ ተአዘዙ ፡ ሎሙ ፤

በደመና ፡ ተሸፍነው ፡ ሊታዩባቸው ፡ በታዘዙላቸው ፡ አዝማናት፡ (ዘመኖች) ፡ በደመና ፡ ተሸፍነው ፡ አይታዩም ። አንድም ፡ ምግባር፡ ትሩፋት ፡ ሊሠሩባቸው ፡ በታዘዙላቸው ፡ አዝማን ፡ (ወራት) ፡ ምግባር ፡ ትሩፋት ፡ ሲሠሩ ፡ አይታዩም ።

፯ ። ወኵሉ ፡ ሥርዓተ ፡ ከዋክብት ፡ ይትዐፀው ፡ ላዕለ ፡ ኃጥአን ።

የከዋክብት ፡ ሥርዓታቸው ፡ በኃጥአን ፡ ይለወጣል ።

ወሕሊናሆሙ ፡ ለእለ ፡ ይነብሩ ፡ ዲበ ፡ ምድር ፡ ይስሕቱ ፡ ዲቤሆሙ ።

በዚህ ፡ ዓለም ፡ የሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ሕሊናቸው ፡ በከዋክብት ፡ ይስታል ፤ ከዋክብትን ፡ ያመልኳቸዋል ።

፰ ። ወይትመየጡ ፡ እምኵሉ ፡ ፍናዊሆሙ ፡ ወይስሕቱ ።

ከአምልኮተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወደ ፡ አምልኮተ ፡ ጣዖት ፡ ይመለሳሉ ። ይስታሉ ።

ወያመስልዎሙ ፡ አማልክተ ።

ከዋክብትን ፡ አማልክት ፡ ያስመስሏቸዋል ።

፱ ። ወይበዝኀ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ እከይ ፡ ወመቅሠፍት ፡ ይመጽእ ፡ ዲቤሆሙ ።

መከራ ፡ ይበዛባቸዋል ። ሁሉንም ፡ ያጠፋቸው ፡ ዘንድ ፡ መቅሠፍት ፡ በእነርሱ ፡ ይመጣል ።

ከመ ፡ ያኅጕሎሙ ፡ ለኵሎሙ ።

ሁሉንም ፡ ያጠፋቸው ፡ ዘንድ ።

፲ ፤ ወይቤለኒ ፡ አ ፡ ሄኖክ ፡ ነጽር
መጽሐፈ ፡ ዘጸፍጸፈ ፡ ሰማይ ፤
ሄኖክ ፡ በሰማይ ፡ ሰሌዳ ፡ የተ
ጻፈውን ፡ እይ ፤ ተመልከት ፡
አለኝ ፤
ወአንበብ ፡ ዘጽሑፍ ፡ ዲቤሆሙ ፡
ወአእምር ፡ ኵሎ ፡ ፩ደ ፡ ፩ደ ፤
አንዱንም ፡ አንዱን ፡ ሰው ፡ ግብ
ራቸውን ፡ እይ ፤ ተመልከት ፡
አለኝ ፤ ግብራቸውም ፡ አካላቸ
ውም ፡ ተጽፏልና ፤
፲፩ ፤ ወነጸርኩ ፡ ኵሎ ፡ ዘበጸፍጸፈ ፡
ሰማይ ፤
በሰማይ ፡ ሰሌዳ ፡ የተጻፈውን ፡
አይቼ ፤
ወአንበብኩ ፡ ኵሎ ፡ ዘጽሑፍ ፡ ወአእ
መርኩ ፡ ኵሎ ፤
የተጻፈውን ፡ ሁሉ ፡ አነበብኩት ፤
ሁሉንም ፡ መርምሬ ፡ አወቅሁ ፤
ወአንበብክዋ ፡ ለመጽሐፍ ወኵሎ ፡
ዘጽሑፍ ፡ ውስቴታ ፤
መጽሐፉቱን ፡ አነበብኋት ፤ በው
ስጧም ፡ የተጻፈውን ፡ ሁሉ ፤
ኵሎ ፡ ምግባሮሙ ፡ ለሰብእ ፡ ወኵሎ፡
ዘሥጋ ፡ ውሉደ ፡ ዘዲበ ፡ ምድር ፤
በዚህ ፡ ዓለም ፡ ያሉ ፡ ሥጋዊ
ደማዊ ፡ የሆኑ ፡ ውሉድን ፡ ሁሉ ፡
ግብራቸውን ፡ ሁሉ ፡ አነበብኩ ፤
እስከ ፡ ትውልደ ፡ ዓለም ፤
ይህ ፡ ዓለም ፡ እስኪያልፍ ፡
ኋረስ ፤

፲፪ ፤ ወእምዝ ፡ ሰቤሃ ፡ ባረክዎ ፡
ለእግዚእ ፡ ዓቢይ ፡ ወንጉሠ ፡ ስብ
ሐት ፡ ዘለዓለም ፡ በከመ ፡ ገብረ ፡
ኵሎ ፡ ግብረ ፡ ዓለም ፤
ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ገናና ፡ የሆነ ፡ የዘ
ለዓለም ፡ ክብር ፡ ያለው ፡ ንጉሥ ፡
እግዚአብሔርን ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ አመሰ
ገንሁት ፤
፲፫ ፤ ወሰባሕክዎ ፡ ለእግዚእ ፡ በእ
ንተ ፡ ትዕግሥቱ ፤
ኃጥአንን ፡ ስለ ፡ ታገሰ ፡ አመሰገ
ንኩት ፤
ወባረኩ ፡ ወበከይኩ ፡ ዲበ ፡ ውሉደ ፡
አዳም ፤
ለጻድቃን ፡ ባደረገው ፡ ክብር ፡
አመሰገንኩት ፤ ይህንንም ፡ ሁሉ
አይቼ ፡ በአዳም ፡ ልጆች ፡ ላይ
አለቀስኩ ፤
፲፬ ፤ ወይእተ ፡ ጊዜ ፡ እቤ ፡ ብፁዕ
ብእሲ ፡ ዘይመውት ፡ እንዘ ፡ ጻድቅ ፡
ወኄር ፤
ለጻድቃን ፡ ያደረገላቸውን ፡ በኃ
ጥአን፡ የተደረገባቸውን ፡ አይቼ፤
ደግ ፡ ቸር ፡ ሰው ፡ እንደሆነ ፡
የሞተ ፡ ንዑድ ፡ ነው ፤ ክቡር ፡
ነው ፡ አልኩ ፤
ወኵሉ ፡ መጽሐፈ ፡ ዓመፃ ፡ ዘኢ
ተጽሕፈ ፡ ዲቤሁ ፤
ተጽሕፈ ፡ ግሥ ፡ ነው ፤ ኃጢአት፡
የሌለበት ፡ ሰው ፤ አንድም ፡

የኃጢአት ፡ ደብዳቤ ፡ ያልተጻፈ
በት ፡ ሰው ፡ ንዑድ ፡ ነው ፤
ክቡር ፡ ነው ፡ አልኩ ፤

ወኢተረክበ ፡ ጌጋይ ፡ በላዕሌሁ ፡
በዕለተ ፡ ኵነኔ ፤

ያን ፡ ጊዜ ፡ በደልም ፡ ከእርሱ ፡
ያልተጻፈበት ፡ ፍርድ ፡ በሚፈረ
ድበትም ቀን ፡ በሱ ፡ የበደል ፡ ሥራ ፡
ያልተገኘበት ፡ ደግ ፡ ሰው ፡ ነው ፤

፲፩ ፤ ወእሙንቱ ፡ ሠለስቱ ፡ ቅዱሳን ፡
አቅረቡኒ ፡ ወአንበሩኒ ፡ ውስተ ፡
ምድር ፡ በቅድመ ፡ ኖኅተ ፡ ቤትየ ፤

የከበሩ ፡ እነዚያም ፡ ሦስቱ ፡ መላ
እክት ፡ በቤቴ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡
አስቀመጡኝ ፤

፲፪ ፤ ወይቤሉኒ ፡ አይድዕ ፡ ኵሎ ፡
ለማቱሳላ ፡ ወልድከ ፤

ለልጅህ ፡ ለማቱሳላ ፡ ይህንን ፡
ሁሉ ፡ ንገር ፤

ወአርኢ ፡ ለኵሉሙ ፡ ውሉድከ ፡ ከመ ፡
ኢይጸድቅ ፡ ኵሉ ፡ ዘሥጋ ፡ በቅድመ ፡
እግዚእ ፤

ሥጋዊ ፤ ደማዊ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡
በጌታ ፡ ፊት ፡ ጻድቅ ፡ ሁኖ ፡
እንደማይገኝ ፡ ለልጆችህ ፡ ሁሉ ፡
አስተምር ፤

እስመ ፡ ውእቱ ፡ ፈጣሪሆሙ ፤

እርሱ ፡ የፈጠራቸው ፡ ነውና ፤
ግብራቸውን ፡ የሚያውቅ ፡ እሱ
ነውና ፤

፲፫ ፤ ፩ደ ፡ ዓመተ ፡ ነኀድገከ ፡ በኀበ ፡
ውሉድከ ፤

በልጆችህ ፡ ዘንድ ፡ አንድ ፡
ዓመት ፡ እንተውሃለን ፡ አሉኝ ፤

እስከ ፡ ካዕበ ፡ ትኤዝዝ ፡ ከመ ፡
ትምህሮሙ ፡ ለውሉድከ ፤

ልጆችህን ፡ ታስተምራቸው ፡
ዘንድ ፤ ዳግመኛ ፡ እስክታዝ ፡
ድረስ ፤ ሳይለይ ፡ ላስተማረው ፡
ካዕበ ፡ አለ ፤

ወትጽሐፍ ፡ ሎሙ ፡ ወታስምዕ ፡
ለኵሎሙ ፡ ውሉድከ ፤

ትጽፍላቸው ፡ ዘንድ ፡ ለልጆችህም ፡
ሁሉ ፡ ታዳኝባቸው ፡ ዘንድ ፡ አንድ ፡
ዓመት ፡ እንተውሃለን ፡ አሉኝ ፤

፲፬ ፤ ወበካልዕ ፡ ዓመት ፡ ይነሥኡከ ፡
እማእከሎሙ ፤

በሁለተኛው ፡ ዘመን ፡ ከእርሳቸው
ይለዩሃል ፤ አንድም ፡ ወካዕበ ፡
ዓመተ ፡ ኾነድገከ ፡ ይላል ፤ ልጆ
ችህን ፡ ታስተምር ፡ ዘንድ ፡
እስክታዝዝ ፡ ድረስ ፡ አንድ ፡
ዓመት ፤ ሁለት ፡ ዓመት ፡ እን
ተውሃለን ፤ ወበካልዕ ፡ ይነሥ
ኡከ ፤ ለ፪ኛው ፡ ሦስተኛውን ፡
ካዕበ ፡ አለው ፤ በሦስተኛው ፡
ግን ፡ ከልጆችህ ፡ ይለዩሃል ፤

ወይጽናዕ ፡ ልብከ ፤

ልቡናህ ፡ በዕውቀት ፡ በሃይ
ማኖት ፡ ይጽና ፤

እስመ ፡ ኅሩያን ፡ ለኅሩያን ፡ ያየድዑ ጽድቀ ፤

መምህራን ፡ ለመምህራን ፡ እውነት ፡ ነገርን ፡ ያስተምራሉና ፤ ይጽናዕ ፡ ልብክ ፡ ላለው ፤

፲፱ ፤ ጻድቅ ፡ ምስለ ፡ ጻድቅ ፡ ይትፌሣሕ ፤

ጻድቅ ፡ የምግባር ፤ የሃይማኖቱን ፡ ዋጋ ፡ አግኝቶ ፡ ከጻድቅ ጋራ ፡ ደስ ፡ ይሰኛልና ፤ ይነሥኡክ ፡ ላለው ፤

ወይትአምኑ ፡ በበይናቲሆሙ ፤

እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ይመሰጋገናሉ ፤

ወኃጥእ ፡ ምስለ፡ ኃጥእ ፡ ይመውት፤

ይህ ፡ ያልጀመረ ፡ ነው ፤ ኃጥእም ፡ ሰው ፡ ከኃጥእ ፡ ሰው ፡ ጋራ ፡ ይሞታል ፤

ወምዩጥ፡ ምስለ ፡ ምዩጥ ፡ ይሰጠም፤

ይህ ፡ ጀምሮ ፡ የተወ ፡ ነው ፤ ጽድቅን ፡ ጀምሮ ፡ወደኃጢአት ፡ የተመለሰ ፡ ሰው ፡ ከጽድቅ ፡ ወደ ፡ ኃጢአት ፡ ከተመለሰ ፡ ሰው ፡ ጋራ ፡ በባሕረ ፡ ገሃነም ፡ ይሰጥማል ፤ እንዲህ ፡ እንዲህ ነውና፡ ብፁዕ ፡ ብእሲ ፡ ላለው ፤

፳ ፤ ወእለ ፡ ይገብሩ ፡ ጽድቀ ፡ ይመውቱ ፡ በእንተ ፡ ምግባረ ፡ ሰብእ ፤

ጽድቅን ፡ የሚሠሩ ፡ ሰዎች ፡ ኃጥአን ፡ የሚሠሩትን ፡ ኃጢአት ፡ ሠርተው ፡ በነፍስ ፡ ይሞታሉ ፤ አንድም ፡ ጻድቃን ፡ የኃጥአን ፡ ዳፋ ፡ ተርፎዋቸው ፡ ይሞታሉ ፤ በአካን ፡ ወልደ ፡ ከርሚ ፡ ምክንያት ፡ ሠላሳ ፡ ስድስት ፡ ሰዎች ፡ እንደሞቱ ፤ አንድም ፡ የኃጥአንን ፡ ኃጢአት አንሥራ ፡ ብለው ፡ ይሞታሉ ፤ እንደ ፡ ሰማዕታት ፤

ወይትጋብኡ ፡ በእንተ ፡ ምግባሮሙ ፡ ለረሲዓን ፤

የረሲዓንን ፡ (የበደለኞችን) ፡ ኃጢአት ፡ ለመሥራት ፡ ይሰበሰባሉ ፤

፳፩ ፤ ወበእማንቱ ፡ መዋዕል ፡ ፈጸሙ፡ እንዘ ፡ ይትናገሩ ፡ ምስሌየ ፤

በእነዚያም ፡ ወራቶች ፡ መላእክት ፡ ከእኔ ፡ ጋር ፡ ተነጋግረው ፡ ጨረሱ ፤

ወቦእኩ ፡ ኀበ ፡ ሰብእየ ፡ እንዘ ፡ እባርኮ ፡ ለእግዚአ ፡ ዓለማት ፤

አራቱን ፡ መዓዝነ ፡ ዓለም ፡ የፈጠረ ፤ ፬ቱን ፡ መዓዝን ፡ አዙሮ ፡ ያሳየኝ ፤ አራቱን ፡ መዓዝን ፡ የሚገዛ ፤ ፬ቱን ፡ መዓዝን ፡ የሚያሳልፍ ፤ እግዚአብሔርን ፡ እያመሰገንኩት ፡ ወደ ፡ ወገኖቼ ፡ ተመለስሁ ።

# ምዕራፍ ፹፪

፩ ፤ ወይእዜኒ ፡ ወልድየ ፡ ማቱሳላ ፡
ኵሎ ፡ እሉንተ ፡ ለከ ፡ እነግር፤
አሁንም ፡ ልጄ ፡ ማቱሳላ ፡ እነ
ዚህን ፡ ሁሉ ፡ ለአንተ ፡ እነግራ
ለሁ ፤
ወጽሕፍ፡ ለከ ፡ ወኵሎ ፡ ከሠትኩ ፡
ለከ ፤
ለአንተም፡ እጽፍልሃለሁ ፤ ሁሉ
ንም፡ ገለጥሁልህ ፡ አለው ፤
፪ ፤ ወወሀብኩከ ፡መጻሕፍቲሆሙ ፡
ለእሉ ኵሎሙ ፤
የእነዚህንም ፡ ሁሉ ፡ መጽሐፎ
ቻቸውን ፡ ሰጠሁህ ፤
ወዕቀብ ፡ ወልድየ ፡ ማቱሳላ ፡ መጻሕ
ፍተ ፡ እዴሁ ፡ ለአቡከ ፤
እኔ ፡ አባትህ ፡ በቃሌ ፡ ያስተማ
ርሁህን ፤ በእጄ ፡ የጻፍኩልህን
ጠብቅ ፤
ወከመ ፡ ተሀብ ፡ ለትውልደ ፡ ዓለም ፤
ለልጅ ፡ ልጅ ፡ ዘመን ፡ ታስተ
ምር ፡ ዘንድ ፤
ጥበበ ፡ ወሀብኩከ ፡ ለከ ፡ ወለውሉድከ ፡
ወለእለ ፡ ይከውኑ ፡ ለከ ፡ ውሉደ ፤
ለአንተ ፡ጥበብን ፡ አስተማርኩህ፡
ካንተም ፡ በኋላ ፡ ለልጆችህ ፡
አስተማርኩ ፤
፫ ፤ ከመ ፡ የሀቡ ፡ ለውሉዶሙ ፡
ወለትውልዳት ፡ እስከ ፡ ለዓለም ፤
እስከ ፡ ዘለዓለሙ ፡ ድረስ ፡ ለል
ጆቻቸው ፡ ያስተምሩት ፡ ዘንድ ፡
አስተማርሁ ፤
ለዛ ፡ ጥበብ ፡ ዲበ ፡ ሕሊናሆሙ ፤
ይህ ፡ ጥበብ ፡ በልቡናቸው ፡
ይጻፍ ፡ ዘንድ ፤
፬ ፤ ወኢይነውሙ ፡ እለ ፡ ይሌብዉ ፡
ወያጸምዑ ፡ በእዝኖሙ ፡ ከመ ፡ ይት
መሀርዋ ፡ ለዛ ፡ ጥበብ ፤
የመምህራን ፤ የመጻሕፍትን ፡
ቃል ፡ ልብ ፡ የሚያደርጉ ፡ ሰዎች ፡
አያርፉም ፡ አያንቀላፉም ፤
ወትደልምሙ ፡ እመባልዕት ፡ ሠናያት
ለእለ ፡ ይበልዑ ፤
ይህችን ፡ ጥበብ ፡ ለሚማሩ ፡
ሰዎች ፡ ከጣቦ ፡ ከግቦ ፡ ይልቅ፡
ትስማማቸዋለች ፤
፭ ፤ ብፁዓን ፡ ጻድቃን ፡ ኵሎሙ ፤
ተምረው ፤ ከግብር ፡ ገብተው ፤
ሥራ ፡ የሠሩ ፡ ሰዎች ፡ ንዑ
ዳን ፡ ክቡራን ፡ ናቸው ፤
ወብፁዓን ፡ ኵሎሙ ፡ እለ ፡ የሐውሩ
በፍኖተ ፡ ጽድቅ ፤
በእውነት ፡ ሥራ ፡ ጸንተው ፡
የሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ባለ ፡ ዘመና

ቸውም ፡ ሁሉ ፡ ቁጥር ፡ ንዑዳን ፡ ክቡራን ፡ ናቸው ።

ወእልበሙ ፡ ኃጢአት ፡ ከመ ፡ ኵሉሙ ፡ ኃጥአን ፡ በኊልቄ ፡ ኵሉ መዋዕሊሆሙ ።

ባለ ፡ ዘመናቸው ፡ ሁሉ ፡ እንደ ኃጥአን ፡ ኃጢአት ፡ የማይሠሩ ሰዎች ፡ ንዑዳን ፡ ክቡራን ፡ ናቸው ። አንድም ፡ ኃጥአን ፡ ባለ፡ ዘመናቸው ፡ ሁሉ ፡ ኃጢአት ፡ እንዲሠሩ ፤ ኃጢአት ፡ የማይሠሩ ፡ ጻድቃን ፡ ንዑዳን ፡ ክቡራን ፡ ናቸው ።

፮ ። ለዘየሐውር ፡ ፀሐይ ፡ በሰማይ።

ዘየሐውር ፡ ሲል ፡ ነው ፤ በሰማይ ፡ የሚሄድ ፡ ፀሐይ ፡ እንዲህ ፡ ነው ።

በአናቅጽ ፡ ይበውእ ።

የሐውር ፡ ያለውን ፡ በአናቅጽ ፡ ይበውእ ፡ ብሎ ፡ አመጣው ። አንድም ፡ ዘየሐውር ፡ ፀሐይ ፡ በሰማይ ፡ በአናቅጽ ፡ ይበውእ ።

ወይወጽእ ፡ ፴ ፡ ዕለተ ፡ ምስለ ፡ አርእስተ ፡ ዐሠርቱ ፡ ምእት ።

በሰማይ ፡ የሚሔድ ፡ ፀሐይ ፡ ይገባል ፡ ይወጣል ። አንድም ፡ በኊልቈ ፡ መዋዕሊሁ ፡ ለዘየሐውር ፡ ፀሐይ ፤ ፀሐይ ፡ በሰማይ ፡ በሚሄድበት ፡ ዘመን ፡ ቊጥር ፡ እንደ ፡ ኃጥአን ፡ ኃጢአት ፡ የሌለባቸው ፡ ጻድቃን ፡ ንዑዳን ፡ ክቡራን ፡ ናቸው ፤ በዓናቅጽ ፡ ይበውእ ፡ በቅጽል ፡ የተናገረውን ፡ ባለቤት ፡ አድርጎ ፡ አመጣው ፤ ይህም ፡ ፀሐይ ፡ በምሥራቅ ፡ ይወጣል ፤ በምዕራብ ፡ ይገባል ። ምስለ ፡ አርእስተ ፡ ዐሠርቱ ፡ ምእት ። ከወር ፡ መጋቢዎች ፡ ጋራ ፡ የሺህ ፡ አለቆችን ፡ ስለ ፡ መሩ ፡ አርእስተ ፡ ፲ቱ ፡ ፪ት ፡ አለ ። አንድም ፡ ከሺህ ፡ አለቆች ፡ ጋራ ፡ ሠላሳ ፡ ቀን ፡ ይገባል ፡ ይወጣል ፡ የተመቸ ፡ ነው ።

፯ ። ዝ ፡ ሥርዐቶሙ ፡ ለከዋክብት ፡ ምስለ ፡ ፬ቱ ፡ እለ ፡ ይትዌስኩ ።

ከወር ፡ መጋቢዎች ፡ ላይ ፡ ከሚጨመሩ ፡ ከ፬ቱ ፡ ከ፲፩ዱ ፡ ከዋክብት ፡ ጋራ ፡ የሚደረግ ። አንድም ፡ በ፲፩ድ ፡ ላይ ፡ ከሚጨመሩ ፡ ካ፬ቱ ፡ ጳጕሜን ፡ ከዋክብት ፡ ጋራ ፡ የሚደረግ ፡ የከዋክብት ፡ ሥርዓታቸው ፡ ይህ ፡ ነው ።

ወእለ ፡ ይሌልዩ ፡ ማእከለ ፡ ፬ቱ ፡ ክፍለ ፡ ዓመት ፡ እለ ፡ ይመርሕዎሙ ።

የሚመግቡባቸው ፡ ፬ቱን ፡ ክፍለ፡ ዘመን ፡ የሚለዩ ፡ ብሎ ፡ ለ፲፩ዱ ቀጸለ ።

፭ ፡ ወምስሌሆሙ ፡ ይበውኡ ፡ ፬ተ ፡ መዋዕለ ፡

ከወር ፡ መጋቢዎች ፡ ጋራ ፡ የ፺፩ዱን ፡ ፬ቱን ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ያወጣሉ ፡ ያገባሉ ፡ አንድም ፡ ከ፺፩ዱ ፡ ጋራ ፡ ፬ቱ ፡ የጳጒሜን ፡ ከዋክብት ፡ ፩ ፡ ቀን ፡ ይወጣሉ ፡ ይገባሉ ፡

በእንቲአሆሙ ፡ ይጌግዩ ፡ ሰብእ ፡

፺፩ዱ ፡ ከዋክብት ፡ ፍጡራን ፡ አይደሉም ፡ ብለው ፡ ሰዎች ፡ ይበድላሉ ፡ አንድም ፡ የ፬ቱን ፡ ጳጒሜን ፡ ከዋክብት ፡ የሉም ፡ ብለው ፡ ይበድላሉ ፡ አይሁድ ፡ እስማኤላውያን ፡ ይሏቸዋልና ፡

ወኢየሐስብዎሙ ፡ በኍላቈ ፡ ኵሉ ፡ ዓለም ፡

በዘመን ፡ ሁሉ ፡ ፍጡራን ፡ ናቸው ፡ ብለው ፡ ፺፩ዱን ፡ አይቈጥሯቸውም ፡ አንድም ፡ አሉ ፡ ብለው ፡ አያስቧቸውም ፡

እስመ ፡ ይጌግይዎሙ ፡

ፍጡራን ፡ አይደሉም ፡ ይሏቸዋልና ፡ አንድም ፡ የሉም ፡ ይሏቸዋል ፡

፮ ፡ ወኢየአምርዎሙ ፡ ሰብእ ፡ ጥንቁቀ ፡

ፍጡራን ፡ እንደ ፡ ሆኑ ፡ ሰዎች ጠንቅቀው ፡ አያስቧቸውም ፡ አያውቋቸውምና ፡ አንድም ፡ እንዳሉ፡ አያውቋቸውምና ፡

እስመ ፡ ሀለዉ ፡ በሐሳበ ፡ ዓመት ፡

በዘመኑ ፡ ቍጥር ፡ አሉና ፡ ፍጡራን ፡ ናቸው ፡ ብለው ፡ አያስቧቸውም ፡ አንድም ፡ በዘመኑ ፡ ቍጥር ፡ አሉና ፡ ምንም ፡ ቢኖሩ ፡ በዘመን ፡ ቍጥር ፡ የሉም ፡ ይሏቸዋል ፡

ወአማን ፡ ልኩዓን ፡ እሙንቱ ፡ ለዓለም ፡

በእውነት ፡ የተጻፉ ፡ ናቸውና ፡

፯ ፡ ፩ዱ ፡ በቀዳሚ ፡ ኆኅት ፡

አንዱ ፡ በመጀመሪያዪቱ ፡ መስኮት ፡ ይገባል ፡ ጥቅምት ፡ ኅዳር ፡ ታኅሣሥ ፡ ሲያልቅ ፡ ፩ ፡ ጳጒሜን ፡ አለችና ፡

ወ፩ዱ ፡ በሣልሲት ፡ ኆኅት ፡

አንዱ ፡ በሦስተኛዪቱ ፡ መስኮት ፡ ጥር ፡ የካቲት ፡ መጋቢት ፡ ሲያልቅ ፡ ፩ድ ፡ ጳጒሜን ፡ አለችና ፡

ወ፩ዱ ፡ በራብዕ ፡ ኆኅት ፡

አንዱ ፡ በአራተኛዪቱ ፡ መስኮት ፡ ሐምሌ ፡ ነሐሴ ፡ መስከረም ፡ ሲያልቅ ፡ ፩ድ ፡ ጳጒሜን ፡ አለችና ፡

ወ፩ዱ ፡ በሳድስ ፡ ኆኅት ፡

አንዱ ፡ በስድስተኛዪቱ ፡ መስኮት ፡ ይገባል ፡ ሚያዝያ ፡ ግንቦት ፡ ሰኔ ፡ ሲያልቅ ፡ ፩ድ፡ ጳጒሜን ፡ አለና ፡ ዳርና ፡ ዳሩን ፡ ተናግሮ ፡ ተወ ፡ ዳርና ፡ ዳሩ ፡ ከታወቀ ፡ መካከሉም ፡ አይጠፋም ፡ ብሎ ፡ ነው ፡

፲፩ ፤ ወይትፌጸም ፡ ዓመት ፡ በመዋዕል ፡ ፫፻ወ፷ወረቡዕ ፤
፫፻፷፬ቱን ፡ ቀን ፡ አንድ ፡ እያሉ ፡ ዘመን ፡ ይፈጸማል ፤
ወአማን ፡ ነገሩ ፡ ወጥንቁቅ ፡ ሐሳቡ ዘልኩዕ ፤
ነገሩ ፡ እውነት ፡ ነው ፤ የተጻፈውም ፡ ቊጥሩ ፡ ጥንቁቅ ፡ ነው ፤
፲፪ ፤ እስመ ፡ ለብርሃናት ፡ ወለአውራኅ ፤ ወለበዓላት ፤ ወለክራማት ፡ ወለመዋዕል ፡ አርአየኒ ፤
ለብርሃናት ፤ ለወሮች ፤ ለበዓላት ፤ ለ፬ቱ ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፤ ለሦስት ፡ መቶ ፡ ስሳ ፡ አራት ፡ ቀኖች ፡ ተሹሟልና ፡ አሳየኝ ፤
፲፫ ፤ ወነፍሐ ፡ ዲቤየ ፡ ዑርኤል መልአክ ፡ ዘአዘዘ ፡ ሊተ ፡ እግዚእ ፡ ኵሉ ፡ ፍጥረት ፤
ዓለምን ፡ የፈጠረ ፤ የሚገዛ ፤ ጌታ ፡ ያዘዘልኝ ፡ ዑራኤል ፡ እውቀትን ፡ አሳደረብኝ ፤
በኃይለ ፡ ሰማይ ፤
በሰማይ ፡ ሠራዊት ፤ በፀሐይ ፤ በጨረቃ ፤ ተሹሟልና ፤
፲፬ ፤ ወሥልጣን ፡ ቦቱ ፡ በመዓልት፡ ወበሌሊት ፡ ውስተ ፡ ሰማይ ፤
በመዓልትም ፡ በሌሊትም ፡ ምግብና ፡ ያለው ፤
ከመ፡ ያርኢ ፡ ብርሃነ ፡ ዲበ፡ ሰብእ ፤
በሰማይ ፡ ለሰው ፡ ብርሃንን ፡ ያሳይ ፡ ዘንድ ፤
ፀሐየ ፡ ወወርኀ ፡ ወከዋክብተ ፤
ብርሃን ፡ ያለውን ፡ ፀሐየ ፡ ወወርኀ ፡ ብሎ ፡ አመጣው ፤
ፀሐይ ፡ ጨረቃ ፡ ከዋክብትን ፤
ወኵሎሙ ፡ ሥልጣናተ ፡ ሰማይ ፤
በግብራቸው ፡ ሥልጣናት ፡ አላቸው ፤ አንድም ፡ ሥሉጣን ፡ ሲል ፡ ነው ፤ አንድም ፡ ሥልጣናትም ፡ የሚባሉ ፡ ከዋክብት አሉና ፤
እለ ፡ ይትመየጡ ፡ በክበቦሙ ፤
በዓውዶሙ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ በዓውዳቸው ፡ በአካሔዳቸው ፡ የሚመላለሱ ፤

ጉባኤ

፲፭ ፤ ወዛቲ ፡ ይእቲ ፡ ሥርዐተ ፡ ከዋክብት ፡ እለ ፡ የዐርቡ ፡ በመካናቲሆሙ ፤ ወበአዝማናቲሆሙ ፤ ወበበዓላቲሆሙ ፤ ወበአውራኂሆሙ ፤
በቦታቸው ፤ በዘመናቸው ፤ በሱባዔያቸው ፡ በወሮቻቸው ፡ የሚወጡ ፤ የሚገቡ ፤ የከዋክብት ፡ ሥርዓት ፡ ይህች ፡ ናት ፤ ፩ድ ፡ አርእስት ፡ ነው ፤
፲፮ ፤ ወእሉ ፡ አስማቲሆሙ ፡ ለእለ ይመርሕዎሙ ፡ ለእለ ፡ የዐቅቡ ፡ ወይበውኡ ፡ በአዝማኒ ፡ ዚአሆሙ ፡ ወበሥርዓታቲሆሙ ፡ ወበጊዜያቲሆሙ ፡ ወበአውራኂሆሙ ፤
ሥርዓታቸውን ፡ የሚጠብቁ ፤ የወር ፡ መጋቢዎች ፡ ከዋክብ

ትን ፡ የሚመሩ ፡ የ፲፻ዱ ፡ ስማ ቸው፡ እሊህ ፡ ናቸው ፤ ፪ት ፡ አር ስት ፡ ነው ፤

ወበሥልጣናቲሆሙ ፤
በየምግብናቸው፤(በየሹመታቸው)

ወበምቅዋማቲሆሙ ፤
በየሠረገላቸው ፤ (በየመቋሚያ ቸው) ፡ በየሥርዓታቸው ፡ የሚ መግቡ ፡ የ፲፻ዱ ፡ ስማቸው ፡ ይህ፡ ነው ፤

፲፫ ፤ ፬ቱ ፡ መራሕያኒሆሙ ፡ ይበ ውኡ ፡ ቀዳሚ ፡ እለ ፡ ይሌልዩ ፡ አር ባዕተ ፡ ክፍለ ፡ ዓመት ፤
በመጀመሪያ ፡ ፬ቱን ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ የሚለዩ ፤ የወር ፡ መጋ ቢዎችን ፡ የሚመሩ ፤ የ፲፻ዱ መጋቢዎች ፡ ከዋክብት ፡ አስቀ ድሞ ፡ ይገባሉ ፤ ሥርዓት ፡ ላለው ፡ አመጣ ፤

፲፬ ፤ ወእምድኅሬሆሙ ፡ ፲ቱ ፡ ወ፪ቱ፡ መራሕያን ፡ ሥርዓታት ፤
ከ፲፻ዱ ፡ በኋላ ፡ ሥርዓታት ፡ ያላቸው ፡ ከዋክብትን ፡ የሚ መሩ ፡ ሥርዓት ፡ ያላቸው ፡ ፲፪ት ፡ ከዋክብት ፡ ይገባሉ ፤

እለ ፡ ይሌልይዎሙ ፡ ለአውራኅ ፤
፲፪ቱን ፡ ወር ፡ የሚለዩ ፤

ወለዓመት ፡ ፫፻ወ፷ወ፬ ፤
፫፻፷፬ ፡ ቀን ፡ የሚሆን ፡ ዓመ ቱን ፡ የሚለዩ ፤

ምስለ ፡ አርእስተ ፡ ፲ቱ ፡ ፻ት፤
ከሽሕ ፡ አለቆች ፡ ጋራ ፤

እለ ፡ ይፈልጥዎሙ ፡ ለመዋዕል ፤
ዕለታትን ፡ የሚለዩ ፡ ብሎ ፡ ለሽሕ ፡ አለቆች ፡ ቀጸለ ፤

ወለ፬ቱ ፡ እለ ፡ ይትዌሰኩ ዲቤሆሙ ፤
በ፫፻፷ ፡ ላይ ፡ የሚጨመሩ ፡ ፬ቱን ፡ ጳጉሜን ፡ የሚለዩ ፡ ብሎ ፡ ለሺህ ፡ ቀጸለ ፤

እለ ፡ ይፈልጡ ፡ መራያኅን ፡ ፬ተ መክፈልተ ፡ ዓመታት ፤
፬ቱን ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ የሚለዩ የወር ፡ መጋቢዎችን ፡ የሚመሩ ፡ ፲፻ድ ፡ ከዋክብት ፡ በሚለዩዋቸው፡ በ፫፻፷፡ቀን ፡ ላይ፡ የሚጨመሩ ፡ ፬ቱን፡ጳጉሜን ፡ የሚለዩ፡ብሎ፡ ለሽህ ፡ ቀጸለ ፤

፲፭ ፤ ወእሙንቱ ፡ አርእስተ ፡ ፲ቱ ፡ ፻ት ፡ ማእከለ ፡ መራሒ ፡ ወተመራሒ ፤
እሊህ ፡ የወር ፡ መጋቢዎች ፡ በመሪና ፡ በተመሪ ፡ መካከል ፡ ናቸው ፤ መሪ ፡ የወር ፡ መጋቢ ዎችን ፡ የሚመሩ ፤ የ፲፻ዱ ፡ መጋቢዎች ፡ ናቸው ፤ ተመሪ ፡ የሽሑ ፡ ናቸው ፤ የወር ፡ መጋ ቢዎች ፡ ይመሯቸዋልና ፤ አን ድም ፡ አርእስተ ፡ ፲ቱ ፡ ፻ት ፡ ማለቱ ፡ የሽሑን ፡ አለቆች ፡ ስለ መሩ ፡ ነው ፤ አንድም ፡ መራሒ ፡ ወተመራሂ ፡ ይላል ፤ እሊህ ፡

የወር ፡ መጋቢዎች ፡ መሪ ፡ ተመሪ ፡ ናቸው ፤ መሪ ፡ አላቸው ፡ የሽሑን ፡ አለቆች ፡ ይመራሉና ፤ ተመሪ ፡ አላቸው ፤ የ፺፩ዱ ፡ መጋቢዎች ፡ ይመሯቸዋልና ፤ አንድም ፡ ማእከለ ፡ መራሒ ፡ ወተመራሂ ፤ እሊህ ፡ የሽሕ ፡ አለቆች ፡ በመሪና ፡ በተመሪ ፡ መካከል ፡ ናቸው ፤ መሪ ፡ የወር ፡ መጋቢዎች ፡ የሽሑን ፡ ይመራሉና ፤ ተመሪ ፡ የዕለት ፡ መጋቢዎችን ፡ የሽሑ ፡ አለቆች ፡ ይመሯቸዋልና ፤ አንድም ፡ መራሒ ፡ ወተመራሒ ፡ ይላል ፤ እሊህ ፡ የሽሕ ፡ አለቆች ፡ መሪ ፡ ተመሪም ፡ ናቸው ፤ መሪ ፡ አላቸው ፡ የዕለት ፡ መጋቢዎችን ፡ ይመራሉና ፤ ተመሪ ፡ አላቸው ፡ የወር ፡ መጋቢዎች ፡ ይመሯቸዋልና ፤

ወይትዌለክ ፡ ፩ዱ ፡ በድኅረ ፡ ምቅዋም ፤

አንዱ ፡ ከቆመ ፡ በኋላ ፡ ፩ዱ ፡ ይቆማል ፤ ማለት ፡ በአንዱ ፡ ምግብና ፡ አንዱ ፡ ይመግባል ፤ በአንዱ ፡ መንገድ ፡ አንዱ ፡ በሄደበት ፡ አንዱ ፡ ይሄዳል ፤ የ፺፩ዱ ፡ መጋቢ ፡ በሄደበት ፡ የ፺፩ዱ ፡ ይሄዳል ፤

ወመራሕያኒሆሙ ፡ ይፈልጡ ፤

የወር ፡ መጋቢዎችን ፡ የሚመሩ የ፺፩ዱ ፡ ፬ቱን ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ይለያሉ ፤ አንድም ፡ የሽሕ ፡ አለቆችን ፡ የሚመሩ ፡ የወር ፡ መጋቢዎች ፡ አውራኀን ፡ ይለያሉ ፤ አንድም ፡ የዕለት ፡ መጋቢዎችን ፡ የሚመሩ ፤ የሽሕ ፡ አለቆች ፡ ዕለታትን ፡ ይለያሉ ፤

፲ ፤ ወእሉ ፡ አስማቲሆሙ ፤ ለመራሕያኒሆሙ ፡ እለ ፡ ይፈልጡ ፡ ፬ተ ፡ መክፈልተ ፡ ዓመት ፤ እለ ፡ ሥሩዓን ፤

የተሠሩ ፡ ፬ቱን ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ የሚለዩ ፤ የወር ፡ መጋቢዎችን ፡ የሚመሩ ፤ የ፺፩ዱ ፡ ከዋክብት ፡ ስማቸው ፡ እሊህ ፡ ናቸው ፤ ሥርዓተ ፡ ከዋክብት ፡ ላለው ፡ ጨርሶ ፤ ወእሉ ፡ አስማቲሆሙ ፡ ላለው ፡ አመጣ ፤

፲፩ ፤ ምልክኤል ፤ ወሕልመልሜሌክ ፤ ወሚልኤል ፤ ወናርኤል ፤

ሕልመልሜሌክና ፡ ምልክኤል ፡ ናርኤልና ፡ ሚልኤል ፡ ናቸው ፤ ከዋክብቱ ፡ የታዘዙ ፡ ያልታዘዙ ፤ ዕለታቱ ፡ የተጻፉ ፤

፲፪ ፤ ወአስማቲሆሙ ፡ ለእለ ፡ ይመርሕዎሙ ፡ አድርናኤል ፡ ወኢየሱሳኤል ፡ ወኢይሉማኤል ፤

የ፺፩ዱ ፡ ከዋክብት ፡ የሚመሯቸው ፡ የወር ፡ መጋቢዎች ፡ ስማቸው ፡ አድርናኤል ፡ ነው ፤ አንድም ፡ የበታቾቻቸውን ፡ የሽህ ፡ አለቆችን ፡ የሚመሩ ፡ የወር ፡

መጋቢዎች ፡ ስማቸው ፡ አድር ናኤል ፡ ኢየሱሳኤል ፡ ኢይሉ ማኤል ፡ ናቸው ።

፳፫ ፤ እሉ ፡ ፫ቱ ፡ እለ ፡ ይተልዉ ፡ ድኅሬሆሙ ፡ ለመራሕያን ፡ ሥርዓታት ፤ ሥርዓታት ፡ የሚባሉ ፡ ሥር ዓት ፡ ያላቸውን ፡ ከዋክብትን ፡ የሚመሩ ፡ ሥርዓት ፡ ባላቸው ፡ በእሊህ ፡ በ፺፩ዱ ፡ ከዋክብት ፡ ኋላ ፡ የሚከተሉ ፡ ሦስቱ ፡ እሊህ ፡ ናቸው ።

፳፬ ፤ ወ፩ዱ ፡ ዘይተሉ ፡ ድኅሬ ፡ ፫ቱ ፡ መራሕያነ ፡ ሥርዓታት ፤ ሥርዓታት ፡ የሚባሉ ፡ ሥርዓት ፡ ያላቸውን ፡ ከዋክብት ፡ በሚመሩ ፡ ሥርዓት ፡ ባላቸው ፡ በሊህ ፡ በሦ ስቱ ፡ ኋላ ፡ የሚከተል ፡ አንዱም ፡ አንዱም ፡ የሽሕ ፡ አለቃ ፡ አለ ፤ እለ ፡ ይተልዉ ፡ ድኅረ ፡ እልክቱ ፡ መራሕያነ ፡ ምቅዋማት ፡ እለ ፡ ይፈልጡ ፩ተ ፡ ክፍለ ፡ ዓመት ፤ ድኅረ ፡ ፫ቱ ፡ መራኅያነ ፡ ሥርዓ ታት ፡ ላላቸው ፡ ለወር ፡ መጋ ቢዎች ፡ ሲቀጽል ፡ ፩ቱን ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ የሚለዩ ፡ ቦታ ሠረገላ ፡ ያላቸውን ፡ ከዋክብት በሚመሩ ፡ ከ፺፩ዱ ፡ ኋላ ፡ የሚ ቆሙ ፡ ብሎ ፡ ቀጠለ ፤ ይህን ሁሉ ፡ ሦስቱን ፡ የወር ፡ መጋቢ ፡ አንዱን ፡ የሽሕ ፡ አለቃ ፡ ለናር ኤል ይሰጧል ።

፳፭ ፤ በቅድመ ፡ ዓመት ፡ ቀዳማዊ ፡ ይሠርቅ ፡ ወይመልክ ፡ ምልክኤል ፤ በመጀመሪያው ፡ ዘመን ፡ በፊት በፊት ፡ ምልክኤል ፡ ይመግ ባል ፤ ሚያዝያ ፤ ግንቦት ፤ ሰኔ ፡ ነው ።

ዘይሰመይ ፡ ስሙ ፡ ተመዓኒ ፤ ስሙም ፡ ተመዓኒ ፡ (ውዑይ) ይባላል ፤ ተመዓኒ ፡ ማለት ፡ ፀሐይ ፡ ማለት ፡ ነው ።

ወፀሐየ ፤ ፀሐይንም ፡ ይባላል ።

፳፮ ፤ ወኵሎሙ ፡ መዋዕላት ፡ ዘበሥልጣኑ ፡ ዚአሁ ፡ ይመልክ ፡ ፺ ወ፩ደ ፡ ዕለተ፤ በምግብናው ፡ የሚመግባቸው ፡ ዘመኑ ፤ ዕለታቱ ፤ ፺፩ ናቸው ።

፳፯ ፤ ወእሉ ፡ ትእምርታተ ፡ መዋ ዕል ፡ እለ ፡ ሀለዉ ፡ ያስተርእዩ ፡ ዲበ ፡ ምድር ፡ በመዋዕለ ፡ ሥልጣኑ ፡ ዚአሁ ፤ በሚመግባባቸው ፡ ወራት ፡ ይታዩ ፡ ዘንድ ፡ ያላቸው ፡ የዕለታቱ ፡ ምልክት ፤ ሐፍ ፡ ወሞቅ ፤ ውኑዘን ፤ ወዝ ፤ ዋዕይ ፤ ኀዘንም ፡ ይሆ ናል ፤ ላብ ፡ ላብ ፡ ሲለው ፡ ያዝናል ፤ ፀዓተ ፡ ክረምት ፡ ነውና ።

፲፰ ፤ ወኵሉሙ ፡ ዕፀው ፡ ይፈርዩ ፡
ወቈጽል ፡ ይወፅእ ፡ በኵሉ ፡ ዕፀው ፤
እንጨቶችም ፡ ሁሉ ፡ ያፈራሉ ፤
በእንጨቶችም ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡
ቅጠል ፡ ይወጣል ፤
ወማዕረረ ፡ ሥርናይኒ ፤ ወጽጌ ፡ ረዳ ፤
ወኵሉ ፤ ጽጌያት ፡ ይጸግዩ፡ በገዳም፤
የስንዴውም ፡ መከር ፡ ጽጌ ፡
ረዳውም ፡ ሌሎች ፡ አበባዎችም
ሁሉ ፡ በምድረበዱ ፡ ያብባሉ ፤
ወዕፀወ ፡ ክረምት ፡ ይየብሱ ፤
በክረምት ፡ የሚለመልሙ ፡ ዛፎ
ችም ፡ ይደርቃሉ ፤
፲፱ ፤ ወእሉ ፡ አስማቲሆሙ ፡ ለመ
ራሕያኒሆሙ ፡ እለ ፡ መትሕቴሆሙ ፡
ብርክኤል ፡ዜልብሳኤል ፤
የ፺፩ዱ ፡ የሚመሯቸው ፡ የወር
መጋዎቢች ፡ ስማቸው ፤ አንድም
የበታቾቻቸውን ፡ የሺሕ ፡ አለቆ
ችን ፡ የሚመሩ ፤ የወር ፡ መጋ
ቢዎች ፡ ስማቸው ፡ ብርክኤል ፤
ዜልብሳኤል ፡ ይባላሉ ፤
ወካልእ ፡ ዘይትዌሰክ ፡ ርእሰ ፡ ፲ቱ ፡
፻ት ፡ ስሙ ፡ ሔሉያሴፍ ፤
ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ የሚጨመር ፡
ስሙ ፡ ሔሉያሴፍ ፡ የሚባል ፡
የሺሕ ፡ አለቆች ፡ አለቃ ፡ ሌላ ፡
ኮከብ ፡ አለ ፤
፳ ፤ ወተፈጸመ ፡ መዋዕለ ፡ ሥል
ጣኑ ፡ ለዝ ፡ ካልእ ፡ መራሒ ፤ ዘድኅ
ሬሆሙ ፡ ሕልሜልሜሌክ ፤

ወተፈጸመ ፡ ሥልጣኑ ፡ ለዝ ፡
ካልእ ፡ መራሂ ፡ ሲል ፡ ነው ፤
ከናርኤል ፡ ከምልክኤል፡ በኋላ ፡
የሚመግብ ፡ የሕልሜልሜሌክ ፡
ዘመኑ ፡ ምግብናው ፡ ደረሰ ፡ ተፈ
ጸመ ፤ የሽሑስ ፡ ኋላ ፡ ይመጣል፡
ብሎ ፡ መዋዕለ ፡ ሥልጣኑ ፡ ለዝ ፤
የምልክኤል፡ዘመኑ ፡ ምግብናው፡
ተፈጸመ፤ከናርኤል፤ከምልክኤል፡
በኋላ ፡ የሚመግብ ፡ ስሙ ፡
ሕልሜልሜሌክ ፡ ነው ፤ የላይኞ
ችን ፡ አንዱን ፡ የወር ፡መጋቢ ፤
አንዱን ፡ የሺሕ ፡ አለቃ ፡
ለምልክኤል ፡ ይሰጧል ፤
ዘይጼውዕዎ ፡ ስሞ ፡ ፀሐየ ፡ ብሩህ ፤
ስሙን ፡ ብሩህ ፡ ፀሐይ ፡ ይሉ
ታል ፤
፳፩ ፤ ወኵሉ ፡ መዋዕለ ፡ ብርሃኑ ፡
፺ወ፩ዱ ዕለት ፤
የሚያበራበትም ፡ ቀን ፡ ሁሉ ፡
ዘጠና ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ነው ፤
ወእሉ ፡ ትእምርታተ ፡ መዋዕል ፡
ዘዲበ ፡ ምድር ፡ ሐሩር ፡ ወየብስ ፤
በዚህ ፡ ዓለም ፡ የሚመግባቸው ፡
የእነዚህ ፡ ወራቶች ፡ ምልክቶች ፡
ድርቅና ፡ ዋዕይ ፡ ናቸው ፤
፳፪ ፤ ወዕፀው ፡ ያወፅኡ ፡ ፍሬሆሙ
ርሱነ ፤ ወብሱለ ፤ ወይሁቡ ፡ ፍሬ
ሆሙ ፡ ይቡሰ ፤

እንጨቶችም ፡ የደረቀውን ፡ የበሰለውን ፡ ፍሬያቸውን ፡ ይሰጣሉ ፤
ወአባግዕ ፡ ይታለዋ ፡ ወይፀንሳ ፤
በጎችም ፡ ይንጠላጠላሉ ፡ ይፀንሳሉ ፤
፴፫ ፤ ወያስተጋብኡ ፡ ኵሉ ፡ ፍሬ ፡ ምድር ፤
ሰዎችም ፡ በዱር ፡ ያለ ፡ የእንጨቱን ፡ ፍሬ ፤
ወኵሉ ፡ ዘሀሉ ፡ ውስተ ፡ ገራውህ ፤
በእርሻውም ፡ ያለ ፡ ፍሬውን ፡ ሁሉ ፤
ወምክያደ ፡ ወይን ፤
በወይኑ ፡ አውድማ ፡ ያለውን ፡ ሁሉ ፡ ይሰበስባሉ ፤
ወይከውን ፡ በመዋዕለ ፡ ሥልጣኑ ፤
በተሾመበትም ፡ ወራት ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ይደረጋል ፤
፴፬ ፤ ወእሉ ፡ እሙንቱ ፡ ስሞሙ ፡ ወሥርዓታቲሆሙ ፤ ወመራሕያኒሆሙ ፡ እለ ፡ መትሕቴሆሙ ፡ ለእሉ ፡ እርእስቲሆሙ ፡ ለ፲፪፡ ጊዳኤል ፡ ወኪኤል ፤ ወሂኤል፤
የ፲፩ዱ ፡ የሚመሯቸው ፡ የወር መጋቢዎች ፡ ስማቸው ፤ አንድም ፡ የበታቾቻቸውን ፡ የሚመሩ ፡ የወር ፡ መጋቢዎች ፡ ስማቸው ፡ ጊዳኤል ፤ ኪኤል ፤ ሂኤል ፡ ይባላሉ ፤ እሊህን፡ ሦስቱን ፡ ለሕልሜልሜሌክ ፡ የወር፡ መጋቢ፡ ይሰጧል፤

ወስሙ ፡ ለዘይትዌሰክ ፡ ምስሌሆሙ ፡ ርእሰ ፡ ፲፪ ፡ አስፋኤል ፤
የወር ፡ መጋቢ ፡ ነው ፤ ርእሰ ፲፪ ፡ ማለቱ ፡ የሽሕ ፡ አለቆችን ፡ ስለመገበ ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ የወር ፡ መጋቢ ፡ ነው ፤ ይህን ፡ አስፋኤልን ፡ ለምልኤል ፡ ይሰጧል ፤
ወተፈጸመ ፡ መዋዕለ ፡ ሥልጣኑ ፡ ዚአሁ ፤
ሦስቱን ፡ የወር ፡ መጋቢ ፤ አንዱን ፡ የሽሕ ፡ አለቃ ፡ ለናርኤል፤ ሁለቱን ፡ የወር ፡ መጋቢ ፡ አንዱን ፡ የሽሕ ፡ አለቃ ፡ ለምልክኤል ፡ ይሰጧል ፤ ሦስቱን ፡ የወር፡ መጋቢ ፡ ለሕልሜልሜሌክ ፡ ይሰጧል ፤ አንዱን ፡ የወር ፡ መጋቢ ፡ ለምልክኤል ፡ ይሰጧል፤አንድም ፡ ሦስቱን ፡ የወር ፡ መጋቢዎች ፡ የናርኤልን ፡ ለምልክኤል ፡ ይሰጧል፤ ሁለቱን ፡ የወር ፡ መጋቢ፡ አንዱን ፡ የሽሕ ፡ አለቃ ፡ አድርጎ ፡ ለራሱ ፡ ለምልክኤል ፡ ይሰጧል ፤ የሕልሜልሜሌክ ፡ ሦስቱን ፡ የወር ፡ መጋቢ ፡ ለራሱ ፡ ይሰጧል ፤ ወአሐዱ ፡ ዘይተሉ ፡ ብሎ፡ አስፋኤል ፡ ያለውን ፡ የሽሕ ፡ አለቃ ፡ አድርጎ ፡ ለሕልሜልሜሌክ ፡ ይሰጧል ፤ ለምልክኤል ሦስቱን ፡ የወር ፡ መጋቢ ፤ ሦስቱን ፡ የሽሕ ፡ አለቃ ፡ ሰጠ፤

ለሕልሜልሜሌክ ፡ ሦስቱን ፡ የወር ፡ መጋቢዎች ፡ ሁለቱን የሽሕ ፡ አለቃ ፡ ሰጠ ፤ ለምል ኤልና ፡ ለናርኤል ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ አላቸው ፤ የእኩሌታውን በእኩሌታ ፡ ማሳየት ፡ ለሄኖክ ፡ ልማዱ ፡ ነው ፤ አንድም ፡ የና ርኤልን ፡ ሦስቱን ፡ የወር ፡ መጋቢዎች ፤ ሦስቱን ፡ አንዱ ፤ አንዱን ፡ ለሦስቱ ፡ ለምልክኤል፤ ለሕልሜልሜሌክ ፤ ለምልኤል ፤ ይሰጧል ፤ ወ፩ ፡ ዘይተሉ ፡ ድኅረ ፤ ሦስቱ ፡ መራሕያን ፡ ያለው ፡ የወር ፡ መጋቢ ፡ ነው ፤ ኋላ ፡ ወስሙ ፡ ለዘይትዌስክ ፡ ምስሌሆሙ ፡ ርእሰ ፡ ፲፪ ፡ አስፋኤል ፡ ብሎ ፡ አመጣው ፤ ይህን ፡ ለናርኤል ፡ ይሰጧል ፤ የምልክኤልን ፡ ሁለቱን ፡ የወር፡ መጋቢ ፡ አንዱን ፡ የሽሕ ፡ አለቃ ፡ አድርጎ ፡ ለራሱ ፡ ለምልክኤል ፡ ይሰጧል ፤ ሦስቱን ፡ የወር ፡ መጋቢ ፡ የራሱን ፡ የሽሕ ፡ አለቃ ፡ አድርጎ ፡ ለሕልሜልሜሌክ ፡ ይሰ ጧል ፤ አንዱን ፡ የወር ፡ መጋቢ ፡ ሦስት ፡ የሽሕ ፡ አለቃ ፡ አድ ርጎ ፡ ለምልክኤል ፡ ይሰጧል ፤ አንዱን ፡ የወር ፡ መጋቢ ፡ ሦስ ቱን ፡ የሽሕ ፡ አለቃ ፡ ለሕልሜ ልሜሌክ ፡ ሰጠ ፤ ለምልኤልና ፡ ለናርኤል ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ የወር ፡ መጋቢ ፡ ብቻ ፡ ሰጠ ፤ ለሁሉም ፡ እንደዚህ ፡ አላቸው ፡ ለማለት ፡ ነው ።

## ምዕራፍ ፹፱ ፤

፩ ፤ ወይእዜኒ ፡ አርአይኩከ ፡ ወል ድየ ፡ ማቱሳላ ፡ ኵሎ ፡ ራዕየ ፡ ዘርኢኩ ፡ እነግር ፡ በቅድሜከ ፤
ዛሬም ፡ ልጄ ፡ ማቱሳላ ፡ ያየ ሁትን ፡ ራእይ ፡ ሁሉ ፡ ገለጽ ኩልህ ፡ ይህንንም ፡ በፊትህ ፤ እናገራለሁ ፤

፪ ፤ ክልኤተ ፡ ራእያተ ፡ ርኢኩ ፡ እንበለ ፡ እንሣእ ፡ ብእሲተ ፤
ሚስት ፡ ሳላገባ ፡ ሁለት ፡ ራእ ዮችን ፡ አየሁ ፤
ወአሐዱሂ ፡ እምኔሆሙ ፡ ኢይትማሰል ፡ ምስለ ፡ ካልኡ ፤
ከእነርሱ ፡ አንዱ ፡ ካንዱ ፡ ጋራ ፡ አይመሳሰልም ፤

፫ ፤ ቀዳማየ ፡ አመ ፡ እትሜሀር ፡ መጽሐፈ ፤
መጀመሪያውን ፡ ራእይ ፡ መጽ ሐፍ ፡ አበውን ፡ በምማርበት ፡ ጊዜ ፡ አየሁ ፤
ወካልእ ፡ ዘእንበለ ፡ እንሥእ ፡ ለእምከ፤ ሁለተኛውን ፡ ራዕይ ፡ ግን ፡ እናትህን ፡ እድናን ፡ ሳላገባ፤

ርኢኩ ፡ ራእየ ፡ ጽኑዐ ፨
የጸና ፡ ራእይን ፡ አየሁ ፨
፫ ፨ ወበእንቲአሆሙ ፡ አስተብቍዕክዎ ፡ ለእግዚእ ፨
ስለነዚህም ፡ ነገሮች ፡ ጌታን ፡ ለመንሁት ፨
ወስኩብ ፡ ክንኩ ፡ በቤተ ፡ መላልኤል ፡ እምሔውየ ፨
በአያቴ ፡ በመላልኤልም ፡ ቤት ፡ ተኝቼ ፡ ሳለሁ ፨
ርኢኩ ፡ በራእይ ፡ ሰማይ ፡ ይትነጸሕ ፨
ሰማይ ፡ ሲወድቅ ፡ ርግፍግፍ ፡ ሲል ፡ አየሁ ፨
ወይትሐየድ ፡ ወይወድቅ ፡ ዲበ ፡ ምድር ፨
አውታሩ ፡ ነፋስን ፡ ሲቀማ ፤ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ሲወድቅ ፤ አየሁ ፨ ይትደሐይ ፡ ቢል ፡ ሲደቅቅ ፡ ሲፈጭ ፡ አየሁ ፨
፬ ፨ ወሶበ ፡ ይወድቅ ፡ ዲበ ፡ ምድር ርኢክዋ ፡ ለምድር ፡ ከመ ፡ ትት ወሐጥ ፡ ውስተ ፡ ቀላይ ፡ ዓቢይ ፨
ወደ ፡ ምድርም ፡ በወደቀ ፡ ጊዜ ምድርን ፡ በታላቅ ፡ ጥልቅ ፡ ውሀ ፡ ስትሰጥም ፡ አየኋት ፨
፭ ፨ ወአድባር ፡ ዲበ ፡ አድባር ፡ ይሰቀሉ ፨
ተራራ ፡ በተራራ ፡ ላይ ፡ ሲጠፉ ፨ አንድም ፡ ልዑላኑ ፡ ከልዑላኑ ፡ ጋራ ፡ ይጠፋሉ ፨
ወአውግር ፡ ዲበ ፡ አውግር ፡ ይሰጠሙ ፨
ኮረብቶች ፡ ከኮረብቶች ፡ ጋራ ፡ ይሰጥማሉ ፨ አንድም ፡ ትሑታኑ ፡ ከትሑታኑ ፡ ጋራ ፡ ይጠፋሉ ፡
ወአዕዋም ፡ ነዋኃት ፡ እምጕንዳቲሆሙ ፡ ይትገዘሙ ፨
ረጃጅሞች ፡ እንጨቶችም ፡ ከግንዳቸው ፡ እየተነቀሉ ፡ ሲወድቁ ፨
ወይትገደፉ ፡ ወይሰጠሙ ፡ ውስተ ፡ ቀላይ ፨
ሲወድቁ ፡ በጥልቅ ፡ ወንዝም ፡ ሲሰጥሙ ፡ አየሁ ፡ አለ ፨
፮ ፨ ወእምኔሁ ፡ ወድቀ ፡ ነገር ፡ ውስተ ፡ አፉየ ፨
ከዚህ ፡ ጥፋት ፡ የተነሣ ፡ በአንደበቴ ፡ ነገር ፡ ተነገረ ፨
ወአንሣእኩ ፡ እጽራሕ ፡ ወእቤ ተነጕለት ፡ ምድር ፨
ምድርም ፡ ጠፋች ፡ ብዬ ፡ እጮህ ፡ ጀመር ፨
፯ ፨ ወመላልኤል ፡ እምሔውየ ፡ አንሥአኒ ፡ እንዘ ፡ አነ ፡ እሰክብ ፡ ኀቤሁ ፨
አያቴ ፡ መላልኤልም ፡ እኔን ፡ በእርሱ ፡ ዘንድ ፡ ተኝቼ ፡ ሳለሁ ፡ አነሣኝ ፨
ወይቤለኒ ፡ ለምንት ፡ ከመዝ ፡ ትጸርሕ ፡ ወልድየ ፨
ልጄ ፡ እንደዚህ ፡ አድርገህ ፡ ለምን ፡ ትጮሃለህ ?
ወለምንት ፡ ከመዝ ፡ ተአወዩ ፨
እንደዚህስ ፡ አድርገህ ፡ ለምን ፡ ታለቅሳለህ? አለኝ ፡አለ ፨

፱ ፤ ወነገርክዎ ፡ ኵሎ ፡ ራዕየ
ዘርኢኩ ፤
እኔም ፡ ያየሁትን ፡ ራእይ ፡ ሁሉ ፡
ነገርሁት ፤
፲ ፤ ወይቤለኒ ፡ ከመ ፡ ጽኑዕ ፡
ርኢከ ፡ ወልድየ ፤
እንደ ፡ ሌላው ፡ ጽኑ ፡ ባለ ፡
አእምሮ ፤ አንድም ፡ ባለ ፡ አእ
ምሮ ፡ እንደ ፡ መሆንህ ፤ አን
ድም ፡ ጽኑዐ ፡ ጽኑዕ ፡ ራእይን ፡
አየህ ፤
ወኃየለ ፡ ራእየ ፡ ሕልምከ ፡ ኀቡእተ ፡
ኵሉ ፡ ኃጢአተ ፡ ምድር ፤
በሰው ፡ ሁሉ ፡ ኃጢአት ፡
የሚደረግ ፡ ረቂቅ ፡ መቅሠፍ
ትን ፡ በሕልምህ ፡ ማየትህ ፡
ጸና ፤ በረታ ፤
ወትሠጠም ፡ ሀለወት ፡ ውስተ ፡
ቀላይ ፡ ወተንጉል ፡ ንጉለ ፡ ዓቢየ ፤
ምድር ፡ በጥልቅ ፡ ውሀ ፡ ትስ
ጥም ፡ ዘንድ ፡ አላት ፤ ጽኑ ፡
ጥፋትንም ፡ ትጠፋለች ፡ አለኝ ፤
፲፩ ፤ ወይእዜኒ ፡ ወልድየ ፡ ተን
ሥእ ፤ ወአስተብቍዖ ፡ ለእግዚአ ፡
ስብሐት ፤
አሁንም ፡ ልጄ ፡ የክብር ፡ ባለ
ቤት ፡ ጌታን ፡ ለምነው ፤
እስመ ፡ መሃይምን ፡ አንተ ፤
አንተ ፡ የታመንክ ፡ ነህና ፤
ከመ ፡ ይትርፍ ፡ ትራፍ ፡ በዲበ ፡
ምድር ፤
በዚህ ፡ ዓለም ፡ የሰው ፡ ዘር ፡
ይቀር ፡ ዘንድ ፤

፲፪ ፤ ወይደመስሳ ፡ ለኵላ ፡ ምድር ፡
ወልድየ ፡ እምሰማይ ፡ ይሄሉ ፡ ዝ ፡
ኵሉ ፡ ዲበ ፡ ምድር ፤
ልጄ ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ መቅሠፍት፡
ከሰማይ ፡ ወርዶ ፡ በዚህ ፡
ዓለም ፡ ይደረጋል ፤
ወዲበ ፡ ምድር ፡ ይከውን ፡ ኀጒል ፡
ዓቢይ ፤
በዚህም ፡ ዓለም ፡ ጽኑ ፡ ጥፋት
ይደረጋል ፤
፲፫ ፤ ወእምኔሁ ፤ ተንሣእኩ ፤ ወጸ
ለይኩ ፤ ወአስተብቋዕኩ ፡ ወሰአልኩ ፤
ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ተነሥቼ ፡
ፈጽሜ ፡ ለመንኩ ፤
ወጸሎትየ ፡ ጸሐፍኩ ፡ ለትውልደ ፡
ዓለም ፤
ልመናዬንም ፡ ለልጅ ፡ ልጅ ፡
ዘመን ፡ ሊሆን ፡ ጻፍኩት ፡ አለ፤
፲፬ ፤ ወኵሎ ፡ አርአይኩከ ፡ ወል
ድየ ፡ ማቱሳላ ፤
ልጄ ፡ ማቱሳላ ፡ ሁሉን ፡ አሳ
የሁህ ፤
ወሶበ ፡ ወጻእኩ ፡ ታሕተ ርኢክዎ ፡
ለሰማይ ፤
ሰማይ ፡ ሲወድቅ ፡ አይቶ ፡
ይጫነኛል ፡ መስሎት ፡ ምድር፡
ምድር ፡ እያለ ፡ መጥቶ ፡
ነበርና ፤
ነጸርክዋ ፡ ለሰማይ ፤
ሰማይን ፡ አየኋት ፡ አለ ፤
ወለፀሐይ ፡ ይወጽእ ፡ እምሥራቅ ፤

ፀሐይንም ፡ ከምሥራቅ ፡ ሲወጣ፡ አየሁት ፤

፲፩ ፤ ወወርኅ ፡ ይወርድ ፡ እም ዓረብ ፤

ጨረቃም ፡ በምዕራብ ፡ ሲገባ ፡ አየሁ ፤

ወውኁዳት ፡ ከዋክብት ፤

ጥቂቶች ፡ ከዋክብትን ፡ አየሁ ፤

ወኵሉ ፡ ምድር ፤

ምድርን ፡ ሁሉ ፡ አየሁ ፤ እን ድም፡ ወሰበ ፡ ወጸእኩ ፡ ታሕተ፤ በመርከብ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ተቀ ምጬ ፤ በሁለተኛው ፡ ዘመን ፡ በወጣሁ ፡ ጊዜ ፡ ሰማይን ፡ አየሁ ፤ ወርኅ ፡ ይወርድ ፡ እምዕራብ ፤ ጨረቃ ፡ በምዕራብ ፡ ሲገባ ፤ ወውኁዳት ፡ ከዋክብት፡ ጥቂት ፡ ከዋክብትን ፤ ወኵሉ ፡ ምድር ፤ ምድርን ፡ ሁሉ ፡ አየሁ ፤ በመ ርከብ ፡ ሳለሁ ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ አላየሁም ፡ ነበርና ፤ በኖኅ ፡ ተገብቶ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤

ወኵሉ ፡ ዘአእመረ ፡ ዲበ ፡ ቀዳሚ ፡ ወባረክዎ ፡ ለእግዚአ ፡ ኵነኔ ፤

ቀድሞ ፡ በመፍጠር ፡ ያወቀ ውን ፡ ሁሉ ፡ አይቼ ፤ የፍርድ ፡ ባለቤት ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመ ሰገንሁት ፤

በቀዳሚ ፡ ገብረ ፡ ያለውን ፡ በመፍጠር ፡ ባወቀ ፡ ጊዜ ፤ እን ድም ፡ በቀዳሚ ፡ ባለው ፡ ላይ ፡ በመፍጠር ፡ ያወቀውን ፡ ሁሉ ፡ አይቼ ፡ አመሰገንኩት ፤

፲፯ ፤ ወሉቱ ፡ ወሀብኩ ፡ ዕበየ ፡ እስመ ፡ አውጽአ ፡ ፀሐየ ፡ እመሳክወ ምሥራቅ ፤

ፀሐይን ፡ ከምሥራቅ ፡ መስኮት አውጥቷልና ፡ ምስጋናን ፡ አቀ ረብኩለት ፤

ወአዕረገ ፡ ወአሥረቀ ፡ ዲበ ፡ ገጸ ፡ ሰማይ ፤

ፀሐይ ፡ ከጽንፈ ፡ ሰማይ ፡ ወደ ፡ ማእከለ ፡ ሰማይ ፡ ወጥቷልና ፡ አበራ ፤

ወተንሥአ ፡ ወየሐውር ፡ ፍኖተ ፡ እንተ ፡ ተርእየት ፡ ሉቱ ፤

ተሠርዐት ፡ ሲል ፡ ነው ፤ በተሠ ራለት ፡ መንገድ ፤ አንድም ፡ እኔ ፡ ባየሁለት ፡ መንገድ ፡ ይኼድ ፡ ዘንድ ፡ መንገድ ፡ ጀመረ ፤

፲፯ ፤ ወአልዐልኩ ፡ እደውየ ፡ በጽድቅ፡ ወባረክዎ ፡ ለቅዱስ ፡ ወለዓቢይ ፤

በእውነትም ፡ ቃሉቼን ፡ ከፍ ከፍ ፡ አድርጌ ፡ ልዩ ፡ ገናና ፡ የሆነ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመ ሰገንሁት ፤

፲፰ ፤ ወነገርኩ ፡ በመንፈስ ፡ አፉየ ፤

ከአፌ ፡ በሚወጣው ፡ ቃል ፡ ተናገርኩ ፤

ወበልሳነ ፡ ሥጋ ፡ እንተ ፡ ገብረ ፡
አምላክ ፡ ለውሉደ ፡ ሰብእ ፡ ከመ ፡
ይትናገሩ፡ ባቲ ፤
ይናገሩባት ፡ ዘንድ ፡ ለሰው ፡
ሁሉ ፡ አምላክ ፡ በፈጠራት ፡
በሥጋዊ ፣ በደማዊ ፡ አንደበት ፡
ምስጋናውን ፡ ተናገርኩ ፤
ወወሀቦሙ ፡ መንፈሰ ፤
ዕውቀትን ፣
ወአፈ ፣
አፍን፣
ወልሳነ፡ ከመ ፡ ይትናገሩ ፡በቱ፣
ይናገሩበት ፡ ዘንድ ፣ የሚናገሩበት ፡
አንደበትን ፡ የፈጠረ ፡ አምላክ ፡
ለእኔም ፡ ፈጥሮልኛልና ፡ ተናገ
ርኩ ፤
፲፱ ፤ ቡሩክ ፡ አንተ ፡ እግዚእ፤
አቤቱ ፡ አንተ ፡ የተመሰገንህ ፡
ነህ ፤
ንጉሥ ፡ ወዓቢይ ፡ ወኃያል ፣
ንጉሥ ፡ ገናና ፡ ኃይለኛ ፣
በዕበየ ፡ ዚእከ ፡ እግዚእ ፡ ኵሉ ፡
ፍጥረተ ፡ ሰማይ ፤
በገናንነትህም ፡ ኃይለኛ ፡ ነህ ፣
በሰማይ ፡ ላለ ፡ ፍጥረት ፡ ሁሉ ፡
ጌታ ፡ አንተ ፡ ነህ ፤
ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ወአምላከ ፡ ኵሉ ፡
ዓለም ፤
ከነገሥታቱ ፡ በላይ ፡ ያለህ ፡
ንጉሥ ፡ አንተ ፡ ነህ ፣ እራቱ ፡
ማዓዝነ ፡ ዓለምንም ፡ የፈጠርክ ፡
አንተ ፡ ነህ ፤

፳ ፤ ወመለኮትከ ፣ ወመንግሥትከ ፣
ወዕበይከ ፡ ይነብር ፡ ለዓለም ፡ ወለዓ
ለመ ፡ ዓለም ፤
አገዛዝህ ፣ መንግሥትህም ፡ ገናን
ነትህም ፡ ለዘለዓለሙ ፡ ፀንቶ ፡
ይኖራል ፤
ወለኵሉ ፡ ትውልደ ፡ ትውልድ ፡
ሥልጣንከ ፤
ሥልጣንህም ፡ ለልጅ ፡ ልጅ ፡
ሁሉ ፡ ነው ፤
፳፩ ፤ ወኵሉሙ ፡ ሰማያት ፡ ምን
ባሪከ ፡ ለዓለም ፣
ሰማዮችም ፡ ሁሉ ፡ ለዘለ
ዓለሙ ፡ መኖሪያህ ፡ ናቸው ፣
ወኵላ ፡ ምድር ፡ መከየደ ፡ እገሪከ ፡
ለዓለመ ፡ ዓለም ፤
ምድርም ፡ ሁሉ ፡ ለዘለዓለሙ ፡
የእግሮችህ ፡ መዘርጊያ ፡ /መረ
ገጫ/ ናት ፤
፳፪ ፤ እስመ ፡ አንተ ፡ ገበርከ ፡ ኵሉ ፣
ወኵሉ ፡ አንተ ፡ ትመልክ ፤
አንተ ፡ ሁሉን ፡ ፈጥረሃልና ፡
አንተ ፡ ሁሉን ፡ ትገዛለህ ፤
ወኢይጸንዐከ ፡ ግብር ፣ ወኢሐዱ ፤
ላድርገው ፡ ካልህ ፡ አንድ ፡ ሥራ ፡
ስንኳ ፡ ተሰኖህ ፡ አይቀርም ፤
አንድም ፡ ሥራ ፡ ደጅ ፡ አይጠ
ናህም ፣
ወአሐቲ ፡ ጥበብ ፡ ኢተኀልፈከ ፤
አንዲት ፡ ጥበብ ፡ ስንኳ ፡ አትሰ
ወርህም ፤
ወኢትትመየጥ ፡ እመንበርታ ፡ ምን
ባሪከ ፡ ወኢእምገጽከ ፤

እንዋወርሀ ፣ ከአንዋወርዋ : አት ሰወርሀም ፤

፳፫ ፤ ወአንተ : ኵሎ : ተአምር : ወትሬኢ ፣ ወትሰምዕ ፤

አንተ : ሁሉን : መርምረህ ፣ ፈጽመህ : ታውቃለህ ፤ ሁሉንም: ትሰማለህ ፣ ሁሉን :መርምረህ : ታውቃለህና ፤

ወአልቦ : ዘይትኃባእ : እምኔከ : እስመ : ኵሉ : ትሬኢ ፤

ከአንተ : የሚሰወር : ነገር : የለም ፤ ሁሉን : ታያለህና ፤

፳፬ ፤ ወይእዜኒ : መላእክተ : ሰማያቲከ : ይኤብሱ ፤

በልዑል : መዓርግ ፣ በደብር : ቅዱስ ፣ በሰማያዊ : ግብር : የነበሩ : ደቂቀ : ሴት : ይበድላሉ ፤ አንድም : ይበድላሉና ፤

ወዲበ : ሥጋ : ሰብእ : ትከውን : መዓትከ : እስከ : ዕለተ : ዓባይ : ኵነኔ፤

ጽኑዕ : ፍርድ : እስከሚደረግባት : እስከ: ዕለተ : ምጽአት : ድረስ: በሥጋዊ ፣ በደማዊ : ሰው : ላይ : ቁጣህ : ትታዘዛለች ፤

፳፭ ፤ ወይእዜኒ : አምላክ : ወእግዚእ: ወንጉሥ : ዓቢይ ፤

አሁንም : ፈጣሪ ፣ ጌታ ፣ ገናና : ንጉሥ : የምትሆን : አቤቱ ፤

አስተበቍዕ ፣ ወእስእል ፣ ከመ : ታቅም : ሊተ : ስእለትየ ፤

ልመናዬን : ታደርግልኝ : ዘንድ እለምናለሁ ፤ አንድም : እለምናለሁና ፤

ከመ : ታትርፍ : ሊተ : ደኃሪተ : ውስተ : ምድር ፤

በዚህ : ዓለም : የሰው : ዘር : ታስቀርልኝ : ዘንድ : እለምናለሁና ፤

፳፮ ፤ ወኢታጥፍዕ : ኵሎ : ሥጋ ሰብእ : ወኢታዕርቃ : ለምድር ፤

ሰውን : ሁሉ : አታጥፋ ፤ ምድርንም :ባድዋን : አታስቀራት ፤ አንድም : እንዳታጠፋት ፤ ባድዋንም : እንዳታስቀራት : እለምንሃለሁና ፤

ወኢይኩን : ኅጕል : ለዓለም ፤

ለዘለዓለሙ: ጥፋት : አይሁን ፣

፳፯ ፤ ወይእዜኒ : እግዚእየ : አጥፍእ : እምዲበ : ምድር : ሥጋ : እንተ : አምዕዐተከ ፤

አሁንም : ጌታዬ : አንተን : ያሳዘነችህን : ሰውነት : ከዚህ : ዓለም : አጥፋ ፤

፳፰ ፤ ወሥጋ : ጽድቅ : ወርትዕ : አቅም ፤

ምግባር : ሃይማኖትን : የምትሠራ: ሰውነትን :ግን : ጠብቅ ፤

ለተክለ : ዘርዕ : ለዓለም፤

ለዘለዓለሙ : ዘር : ሊሆን ፤

ወኢትሰውር : ገጸከ : እምስእለተ : ገብርከ : እግዚእ ፣

አቤቱ : ከእኔ : ከባርያህ : ልመና ፊትህን : አትመልስ ፡፡